# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 329 ሐምሌ 29 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# በወለድ ተመን ላይ የተመሠረተው አዲሱ የገንዘብ ፖሊሲ ምንድነው?

**መስከረም ሰይፉ**

ከሰሞኑ መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ማድረጉ የሚታወቅ ሲሆን ካደረጋቸው ማሻሻያዎች ውስጥም የገንዘብ ፖሊሲው በወለድ ተመን ላይ የተመሠረተ ይሆናል የሚለው ይገኝበታል። በመንግሥት በኩል በተሰጠው መግለጫም ሮምጃው የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፉን ማዘመን ላይ ትኩረት ያደረገ ነው ተብሏል።

የሦስት ዓመቱ የብሔራዊ ባንክ ስትራቴጂክ እቅድ ዝቅተኛና እና የተረጋገጠ የዋጋ ንረት መኖሩን ማረጋገጥ ሲሆን ብሔራዊ ባንክ ከንግድ ባንኮች ጋር በሚያደርገው የንግድ ግብይት በወለድ ተመን ላይ የተመሠረተ የገንዘብ ፖሊሲ ሥርዓት እንዲፈጠር ቅድሚያ እንደሚሰጥ በመግለጫው ላይ ተነስቷል።

በወለድ ተመን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ማሻሻያው ድሃ ተኮር ያስባለው ምንድነው ?

**አዲሱ ገረመው**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻሉን ተከትሎ አዲሱ ፖሊሲ የኑሮ ውድነት ጫናን በምን መልኩ ሊቀርፍ ይችላል የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ ለመሆኑ ማሻሻያው የኑሮ ውድነቱን የሚያባብስ ወይስ የሚቀንስ ነው?

"መንግሥት በለውጡ ማግስት

ማሻሻያው ድሃ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


ፎቶ - ገበሀ ገብሬ

ሻሪ ስፒገል

# ታዳጊ ሀገራት ምርታማነትን ማሳደግ ላይ ማተኮር አለባቸው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ታዳጊ ሀገራት ምርታማነትን ማሳደግ ላይ ማተኮር እንዳለባቸው በተመድ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ክፍል የፋይናንስ ለዘላቂ ልማት ዳይሬክተር ሻሪ ስፒገል ገለጹ።

ሻሪ ስፒገል በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከፍተኛ የብድር ወለድ መጠን ያለባቸው ታዳጊ ሀገራት መበደር የማይችሉ በመሆኑ ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ምርታማነትን ማሳደግ ላይ ማተኮር አለባቸው።

ታዳጊ ሀገራት ሊወጡት በማይችሉበት አዙሪት ውስጥ በመግባታቸው ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሀገራቱን መርዳት እንዳለበት የገለጹት ዳይሬክተሯ፤ በዓለም ላይ ያሉ በርካታ ሀገራት ከጤና፣ ትምህርትና ከረዥም ጊዜ ኢንቨስትመንት ይልቅ ዕዳቸውን ለመክፈል ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

ሰሞኑን በአዲስ አበባ የተካሄደው አራተኛው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ለልማት ቅድመ ኮንፍረንስ ሀገራቱ በልማት ላይ እንዲያተኩሩና የተዛባውን የዓለም የፋይናንስ ሥርዓት ማስተካከል እንዲቻል አስተዋፅዖ እንደሚኖረውም ገልጸዋል።

እ.አ.አ በ2015 በአዲስ አበባ በተዘጋጀው ሦስተኛው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ለልማት ኮንፍረንስ የፀደቀው የአዲስ አበባ አክሽን አጀንዳ በድህነት ቅነሳ፣ አየር ንብረትና አካባቢ ጥበቃ ላይ ያተኮረና ከማኅበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ከሌሎችም የዘላቂ ልማት

ታዳጊ ሀገራት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






አቶ ታደሰ ከበደ

# በኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዢ ሥርዓት 320 ቢሊዮን ብር ግብይት ተፈፅሟል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት በኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓት ከ22 ሺህ በላይ ጨረታዎችን በማውጣት 320 ቢሊዮን ብር ግብይት ተፈፅሟል ሲል የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ።

የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ፕሮጀክት ማናጀር አቶ ታደሰ ከበደ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት በኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዢ ሥርዓት 22 ሺህ 222 ጨረታዎችን በማውጣት 320 ቢሊዮን ብር ግብይት ተፈፅሟል።

የመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት ሲስተም በ2014 ዓ.ም በዘጠኝ ተቋማት በ22 ጨረታዎች ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማ ሆኖ በመገኘቱ ሥራ ላይ እንዲውል መደረጉን አስታውሰዋል።

በ2015 በጀት ዓመት ሰባ አራት ተቋማትን የሲስተሙ ተጠቃሚ በማድረግና ሁለት ሺህ 300 ጨረታዎችን በማውጣት አምሳ ስድስት ቢሊዮን ብር ግዢ ተፈፅሟል ያሉት ማናጀሩ በ2016 በጀት ዓ.ም በተመሳሳይ ወቅት ሃያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ 22 ጨረታዎች በማስተናገድ 320 ቢሊዮን ብር ግብይት ተፈጽሟል ሲሉ ተናግረዋል።

በኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት በአንድ ጨረታ ላይ እስከ አንድ መቶ 50 ተጫራቾችን የማወዳደር፤ የግል ጨረታ ውድድርን መቶ በመቶ የማሳደግ፤ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የጨረታ ፉክክርን 25 በመቶ ከፍ የማድረግ እንዲሁም በአንድ ጨረታ በአማካኝ ስድስት ሺህ ብር የሚወጣውን የወረቀት ወጪ የማስቀረት ሥራ ተሠርቷል ሲሉ አብራርተዋል።

ሲስተሙ የትራንስፖርት ወጪን ማለትም ሰነድ ለመግዛት፤ ማስታወቂያ ለማየት፣ በጨረታ መክፈቻ ለመሳተፍ የሚወጣውን ውጪ እየቀነሰ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

በፊት የነበረው የመንግሥት የወረቀት የንብረት ግዥ ሥርዓትን ግልጸኝነት የጎደለውን ነበር፤ አሁን በግዢ ሥርዓት ላይ ግልጸኝነትን ለማስፈን የኤሌክትሮኒክስ ግዢን ተግባራዊ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ታደሰ፤ በኤሌክትሮኒክስ ጨረታ እያንዳንዱ የፌዴራል ተቋም የግዢ እቅድ፣ የጨረታ ማስታወቂያና ውጤት በአጠቃላይ የግዥ እቅዱን እስከ ውጤቱ በሲስተሙ ፖርታል ለሁሉም ዜጋ ግልጽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

የፌዴራል መሥሪያ ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች፣ ተጫራቾች፣ ኦዲት የሚያደርጉ አካላት፤ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገራት አቅራቢዎች፤ የክልልና የከተማ አስተዳደሮች በኤሌክትሮኒክ ግዢ እየፈፀሙ ነው፤ ከክልልና ከከተማ አስተዳደሮች የሲዳማ ክልልና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለአብነትም ተጠቃሽ ናቸው ብለዋል።

የኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት ከሰው እጅ ንክኪ የፀዳ በመሆኑ በመንግሥት በባሕላዊ የግዢ አሠራር የነበረውን የሰነድ መደበቅ፤ ማጭበርበርና መሰል ችግሮችን መቀነስ አስችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ ታደሰ አያይዘውም፤ በኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት አሸናፊ ተጫራቾች ጨረታውን አሸንፈው እቃ ለማቅረብ የገቡትን ውል የመጣስና የአለማቅረብ ችግር ይስተዋላል፤ ችግሩን በመፍታት የኤሌክትሮኒክስ ግዢን ሥርዓት ለማጠናከር ውል በጣሱ ተጫራቾች ላይ የውል ማስከበሪያውን የመውረስ፣ በማንኛውም የመንግሥት ጨረታ ላይ እንዳይሳተፉ የመከልከል፤ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፤ ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት በጨረታ እንዳይሳተፉ የማደረግ እርምጃ እየተወሰደ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት ምን ያህል ወጪ ማስቀረት እንደተቻለ ጥናት እየተሠራ ነው፤ የጥናቱ ውጤት ሲደርስ ይፋ እናደርጋለን ሲሉ ጠቁመዋል።

# ሁሉን አካታች የሆነው ሀገራዊ ምክክር

**ማሕሌት ብዙነህ**

በሀገሪቱ መሠረታዊና ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጎልተው የሚታዩ የሀሳብ ልዩነቶችና አለመግባባቶችን ለመፍታት በኃይል አማራጭ ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት የማይቻል መሆኑ ይታወቃል። ለዚህም በሀገሪቱ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እና ባለድርሻ አካላት በጋራ ሆነው መሠረታዊና ሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ በመመካከር መግባባት ላይ ለመድረስ የሀገራዊ ምክክር ለማካሄድ ሂደቱን ከጀመረ ሁለተኛ ዓመታትን ተሻግሯል።

ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶም የአዲስ አበባን እና ድሬዳዋ ከተሞችን ጨምሮ በ10 የኢትዮጵያ ክልሎች የምክክሩ ተሳታፊዎችን የመለየት ሥራ ሠርቷል። በአዲስ አበባ ከተማ የአጀንዳ ልየታ የምክክር ምዕራፍ እንዲሁም ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማኅበረሰብ ክፍሎች ተወካዮች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር አጀንዳ የሚሰበሰብበት መድረክ በመካሄድ ላይ ነው።

በጋምቤላ ክልልም በየወረዳው ከሚገኙ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት የሚሳተፉ ተወካዮችን በመምረጥ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ እያካሄደ ይገኛል።

ኮሚሽኑ እያካሄደ ባለው ሥራው ውስጥም ከሁሉም የማኅበረሰብ አካላት የተወጣጡ ተወካዮችን በማሳተፍ የአካታችነት መርሆውን እየተወጣ እንደሚገኝ መመልከት ተችሏል።

በጋምቤላ ክልል እየተካሄደ የሚገኘው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ላይ ከኑዌር ብሔረሰብ ሴቶችን በመወከል እየተሳተፉ የሚገኙት ወይዘሮ ኛባር ባንዳክ እንደሚሉት፤ ምክክሩ ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የተወጣጡ ተወካዮችን ተሳታፊ አድርጓል። የሁሉንም ሀሳብ በማካተት ለጥያቄዎችና ሀሳቦች የጋራ መፍትሔ ለማግኘት ጥረት መደረጉ ችግሮችን በመፍታት ወደ ሠላም ለመመለስ ያስችላል።

የሠላም መደፍረስ ዋነኛ ተጠቂ ከሆኑት የኅብረተሰብ አካላት ውስጥ ሴቶች የሚጠቀሱ ሲሆን በምክክሩ ላይ ለመሳተፍ እድሉን ያገኙ ሴቶች በውይይቱ በጥልቀት በመሳተፍ ችግሮችን መለየትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣት አለባቸው ሲሉም ተናግረዋል።

ወጣት መንግሥቱ ጌታቸው የወጣቶች ዘርፍ ተወካይ ሲሆን በሀገሪቱ ታይቶ በማይታወቅ መንገድ በሚካሄደው የችግር አፈታት ላይ ተሳታፊ በመሆኑ ደስተኛ እንደሆነ ይገልፃል። ምክክሩም ተስፋ ሰጪ ነው ሲል ይናገራል።


የሕዝብ የጋራ ውይይትና ንግግር የጋራ ሠላምን ለመገንባት ጠቃሚ መንገድ ነው የሚለው ወጣቱ፤ ሁሉም የኅብረተሰብ አካል በሀገሪቱ ጉዳይ ላይ ድርሻ እና ድምፅ ስላለው ውይይቱ ፍሬ እንደሚያፈራ አመላካች ነው ይላል።

ይህም የአሠራሩን ግልፀኝነትንና አሳታፊነትን ያሳያል ያለው ወጣት መንግሥቱ፤ እንደወጣት ለሀገሪቱ ሠላም የሚጠበቅበትን ለማበርከት ብሎም አስፈላጊ አጀንዳዎች እንዲቀርቡና ለፍፃሜ እንዲደርሱ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን አስታውቋል።

የጋምቤላ ክልል እስልምና ጉዳይ ተሳታፊ ኡስታዝ ዑስማን በበኩላቸው፤ ምክክሩ ለሀገራዊ አንድነትና መግባባት ሁሉን አቀፍ ፋይዳ አለው ይላሉ።

ኢትዮጵያ ከሁሉም ማኅበረሰብ ክፍል የተገነባች ትልቅ ሀገር ናት የሚሉት ኡስታዝ ዑስማን፤ ምክክሩ ሁሉንም አካቶ መያዙ ለተሻለ መግባባትና የተሻለ ሀገራዊ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንደሚጠቅም ያስረዳሉ።


ከተወካይ መረጣ ጀምሮ እስከ አሁን ያለው ሂደት ከሁሉም የተውጣጣ የማኅበረሰብ ክፍል



ኡስታዝ ኡስማን



ወ/ሮ ኛባር ባንዳክ



ወጣት መንግሥቱ ጌታቸው




ወ/ሮ ኒቢሉ ኡኩታ

አሳታፊ በመሆኑም ፋይዳ ያለው ሀሳብና የማኅበረሰብ ጥያቄዎች ይቀርባሉ ተብሎ የታሰበበት መሆኑን ይናገራሉ።

በሰዎች መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ቁጭ ብሎ መነጋገር የእስልምና ሀይማኖት አስተምህሮ እንደሆነ የሚጠቅሱት ኡስታዝ ኡስማን፤ ለዚህም የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በሰከነ መንገድ መክሮ የተሻለች ኢትዮጵያ ለማየት ሰፊ እድል አለው ብለዋል።

አደራ ተቀብለው ለመሳተፍ የመጡ ተወካዮችም የመጡበትን ማህበረሰብ በሚያመለክት መንገድ በትጋት መሳተፍ እንዳለባቸው ይጠቁማሉ። ይህም ምክክሩ የታለመለትን አላማ የሚመታ ከማድረጉም ባሻገር ፍትሐዊ፣ ገለልተኛና አካታች ውጤት እንዲኖረው ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

አካልጉዳተኞች በየትኛውም አካባቢ ግጭት ሲፈጠር መሮጥም ሆነ እንደልብ መንቀሳቀስ ስለማይችሉ ዋነኛ ተጠቂ ናቸው። በምክክር ሂደቱ ላይ አካል ጉዳተኞች ተሳታፊ መሆናቸው የችግሩን አስከፊነት በማሳየት መፍትሔ እንዲመጣ አስተዋጽኦ ያደርጋል ሲሉ የተናገሩት ደግሞ የጋምቤላ አካል ጉዳተኞች ፌደሬሽን ዋና ሰብሳቢ አቶ ቻን ቦች ናቸው።

በአንድ ሀገር ጉዳይ ላይ ሁሉን ተሳታፊ ማድረግ ኮሚሽኑ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካትም ጉልህ ሚና አለውም ይላሉ።

በምክክሩ ላይ በመሳተፍ አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርስ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ እንዲቀረፍ በማድረግ እንዲሁም ዘላቂ የሀገር ሰላምና አንድነት



አቶ ቻን ቦች

እንዲሰፍን የበኩላቸውን እንደሚወጡ አቶ ቻን ቦች አስታውቀዋል።

በምክክሩ ላይ ከጋምቤላ ንግድ ዘርፍ ተወካይ የሆኑት ወይዘሮ ኒቦሎ ኡኩታ በበኩላቸው፤ ሠላም ሰርቶ ለመግባት ሆነ ለሕይወት ለመኖር አስፈላጊ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

በምክክሩም ለሠላም ቅድሚያ በመስጠት የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ሀሳቦችን በግልፅ መወያየት ሀገራዊ መፍትሄ ለማግኘት ያስችላል ብለዋል።

ዜና

# በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከ426 ሺህ በላይ አዳዲስ ደንበኞች የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት 426 ሺህ 290 አዳዲስ ደንበኞች የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በገጠርና በከተማ 426 ሺህ 290 አዳዲስ ደንበኞችን ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

በ2016 በጀት ዓመት የአዳዲስ ኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚዎች ቁጥር ከባለፈው 2015 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ75 ሺህ 729 ደንበኞች ጭማሪ አሳይቷል ብለዋል።

ተቋሙ በተጠናቀቀው የ2016 በጀት ዓመት 100 የገጠር ከተሞችና መንደሮችን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግ አቅዶ እንደነበር ያስታወሱት አቶ መላኩ፤ 116 አዳዲስ የገጠር ከተሞችንና መንደሮችን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻልና የደንበኞችን እርካታ ለማሳደግ እየተሠራ ነው። በዚህም ፕሮጀክት ተቀርፆ 50 ሺህ ነባር ቆጣሪዎች በስማርት ቆጣሪዎች በመቀየር ላይ ይገኛሉ።

እስካሁን 36 ሺህ 700 ነባር ቆጣሪዎችን በስማርት ቆጣሪዎች መቀየር ተችሏልም ብለዋል። ነባር ቆጣሪዎቹ በስማርት ቆጣሪ የመቀየሩ ሥራ በተለይ አገልግሎቱን ለማዘመን ከፍተኛ ሚና እንዳለው ተናግረዋል።

በተያዘው በጀት ዓመትም የኤሌክትሪክ ተጠቃሚው ቁጥር ለማሳደግና አገልግሎቱ አሰጣጡ የበለጠ ለማዘመን ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ ነው አቶ መላኩ ያብራሩት።

በበጀት ዓመቱ በተቋሙ አዳዲስ ደንበኞች ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማስቻል በተጨማሪም የተበላሹ የኤሌክትሪክ ማሰራጫ ማዕከላት እድሳት መደረጉን አክለዋል።

ኤሌክትሪክ በማይደርስባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች የሌሎች የኃይል አማራጭ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አስረድተዋል።



ዶክተር ዮሐንስ ኮስትር



ዶክተር ሚሊዮን ደቻሳ



ሲስተር አስገደች ጋሻው

# ማኅበረሰቡ በክረምት ለሚከሰቱ በሽታዎች እንዳይጋለጥ የመከላከል ሥራ ሊሠራ ይገባል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ማኅበረሰቡ በክረምት ወቅት ለሚከሰቱ በሽታዎች እንዳይጋለጥ ራሱን ለበሽታ ከሚያጋልጡ ነገሮች መጠበቅና የመከላከል ሥራ ሊሠራ ይገባል ሲሉ የጤና ባለሙያዎች ተናገሩ።

የማኅበረሰብ ጤና ባለሙያው ዶክተር ዮሐንስ ኮስትር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ማኅበረሰቡ በክረምት ወቅት ለሚከሰቱ በሽታዎች እንዳይጋለጥ ራሱን ለበሽታ ከሚያጋልጡ ነገሮች መጠበቅና የመከላከል ሥራ ሊሠራ ይገባል።

በክረምት ወቅት ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ማለትም የሳንባ፣ የመተንፈሻ አካላት፤ የጉንፋንና የወባ በሽታዎች በብዛት ተከስተው ለማኅበረሰቡ የጤና ስጋት የሚሆኑበት ጊዜ ነው ብለዋል።

በክረምት ወቅት ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በአብዛኛው የሚከሰቱ ቢሆንም የመተንፈሻ አካል ላይ የሚከሰቱ በሽታዎች በሰዎች ላይ የመከሰትና የጤና ችግር የማድረስ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

በክረምት ወቅት በደረቅና በፈሳሽ ቆሻሻዎች እንዲሁም በሌላ ነገሮች የአካባቢ ብክለት ስለሚከሰት ተላላፊ የሆኑና ያልሆኑ በሽታዎች የጤና ስጋት የሚሆኑበት ሁኔታ ከፍተኛ ነው ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ ማኅበረሰቡ በክረምት ወቅት ከሚከሰቱ በሽታዎች ራሱን ለመከላከል የግል፤ የቤተሰብና የአካባቢን ንፅሕና የመጠበቅ ሥራ ሊሠራ ይገባል ብለዋል።

የጤና ባለሙያዎች ስለጤና አጠባብቅ ዜጎችን የማስተማር፤ ማኅበረሰቡም ለወባና ለመተፈሻ አካል በሽታ የሚያጋልጡ ቦታዎችን የማፅዳት ኃላፊነቱን በመወጣት በክረምት የሚከሰቱ በሽታዎችን ሊከላከል ይገባል ሲሉ አመላክተዋል።

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሕክምና ኮሌጅ የሕፃናት ስፔሻሊስት ሐኪምና የሕፃናት ሕክምና ትምህርት ኃላፊ ዶክተር ሚሊዮን ደቻሳ በበኩላቸው፤ የክረምት ወቅትን ተከትለው የሚመጡ በሽታዎች አብዛኛው ተላላፊ በመሆናቸው ማኅበረሰቡ ጤንነቱን ሊጠብቅ ይገባል።

ወባ፤ ውሀ ወለድ፣ የአንጀት ሕመሞች ማለትም ጃርዲያ፣ አሚባ፤ አተት በአጠቃላይ ከእጅ ወደ አፍ በሚደረግ ንክኪ የሚከሰቱ በሽታዎች በክረምት ወቅት ለማኅበረሰቡ ጤና አስጊ ናቸው ብለዋል።

ማኅበረሰቡ የአካባቢውንና የግል ንፅሕናውን መጠበቅ ማለትም፣ የአቆሩ የውሀ ኩሬዎችን በማፋሰስ፣ የፍሳሽ አወጋገድን ማስተካከልና የሽንት ቤት አጠቃቀሙን በማዘመን በሽታዎች እንዳይያዝ ራሱን መከላከል አለበት ሲሉ ተናግረዋል።

በክረምት ወቅት የሚከሰቱ በሽታዎች በማኅበረሰቡ የጤና ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የቅደም መከላከል ሥራ ሊሠራ ይገባል ሲሉ ሲስተር አሰገደች ጋሻው ተናገሩ።

የውሀ ወለድ፤ አተት፣ አስም፤ ሳይነስ፤ የወባና የጉንፋን በሽታዎች በክረምት ወቅት በብዛት ተከስተው በማኅበረሰቡ ዘንድ የጤና ቀውስ የሚያስከትሉ ናቸው ያሉት ሲስተር አሰግድ፤ ማኅበረሰቡ የአለባበስ ባሕሉን በማስተካከል፤ የአካባቢውንና የግሉን ንፅሕና በመጠበቅ፣ ውሀ አፍልቶ በመጠጣት ጤንነቱን ሊጠብቅ ይገባል ብለዋል።

የማኅበረሰቡ የአመጋገብ ሥርዓት መዛባት፤ ስለጤና አጠባበቅ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆንና የሚመለከተውም አካል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በተገቢው መንገድ ባለመሠራቱ ማኅበረሰቡ ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ተጋለጫ የመሆን ዕድሉ እያደገ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ማኅበረሰቡ ከተላላፊና ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ነፃ እንዲሆን የአመጋገብ ሥርዓትን የማስተካከል፤ የአካል እንቅስቃሴ መስራት፣ የአካባቢውንና የግል ንፅሕናውን መጠበቅ፤ የሕመም ስሜት ሲሰማው በአቅራቢው ወደሚገኝ የጤና ጣቢያ በመሄድ የሕክምና አገልግሎትና የባለሙያ ምክር ማግኘት አለበት ሲሉ መልክት አስተላልፈዋል።

# በክልሉ ከአስራ ሁለት ሚሊዮን በላይ ሰዎች የጤና መድኅን አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ከአስራ ሁለት ሚሊዮን በላይ ሰዎች የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የክልሉ ጤና ቢሮ አስታወቀ።

የአማራ ክልል ጤና ቢሮ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሲስተር ክሽን ወልዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በክልሉ የጤና መድኅን ተጠቃሚዎች ቁጥርን ለማሳደግ ሰፊ ሥራ የተሠራ ሲሆን በዚህም በክልሉ ውስጥ ከ12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ ሕዝብ በጤና መድኅን ታቅፎ አገልግሎት እያገኘ ነው።

ከዚህም በ2016 በጀት ዓመት ለሁለት ሚሊዮን 830 ሺህ 867 ሰዎች የምዝገባና እድሳት አገልግሎት የተሰጠ መሆኑን ጠቅሰው፤ 218 ሺህ 406 በአዲስ የተመዘገቡ የጤና መድኅን አባላት እንዲሁም ሁለት ሚሊዮን 612 ሺህ 461 አባወራዎች የነባር የአባልነት ዕድሳት አገልግሎት ያደረጉ መሆኑን ገልፀዋል።

አገልግሎቱንም በሁሉም በክልሉ ባሉ ዞኖች የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በስፋት የተሠራ መሆኑን ሲስተር ክሽን ገልፀው፤ ባለፈው በጀት ዓመትም በወልቃይት ጠገዴ ዞን እና በጠለምት ባሉ ሁሉም ወረዳዎች የጤና መድኅን አገልግሎት ለማስጀመር ጥረት ተደርጓል ብለዋል።

በተጨማሪም በክልሉ ለ 578 ሺህ 661 መክፈል ለማይችሉ አባወራዎች በክልሉና የወረዳው መንግሥት ወጭ በመደጎም አባል እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን ለዚህም ከ513 ሚሊዮን 879 ሺህ 538 ብር ድጎማ ተደርጓል ብለዋል።

እንዲሁም ከከፋይ የጤና መድኅን አባላት ብቻ ሁለት ቢሊዮን 72 ሚሊዮን 507 ሺህ 843 ብር የተሰበሰበ መሆኑንም ገልፀው፤ ከተናጠል ድጎማ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላላ ድጎማ በአጠቃላይ ከሦስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉን አስታውቀዋል።

በክልሉ ከተከሰተው የፀጥታ ችግር ጋር ተያይዞ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት አፈፃፀም ጋር ተያይዞ ዝቅተኛ መሆን፤ በጤና ተቋማት የአገልግሎት ሙሉ አለመሆን፣ የሕክምና የግብዓት እጥረት፣ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ ድጋፍ ለማድረግ አለመቻል ያጋጠመ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ገልፀዋል።

ይህንንም ተግዳሮት ለመፍታትም ከአመራሩ ጋር በመነጋገር የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር ማወያየት፣ ለሕዝቡ ግንዛቤ መፍጠር፣ በየአቅራቢያው ባለው ባንክ ክፍያ በመክፈል መታወቂያ እንዲታደስላቸው የማድረግ ሥራ መሠራቱን ገልፀዋል።

በመሆኑም በቀጣይ በጀት ዓመት በተሻለ መልኩ በክልሉ ውስጥ ወደ አራት ሚሊዮን 593 ሺህ 820 የሚሆኑ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን አባላትን በአዲስ እና በነባር ለማፍራት የታቀደ መሆኑን ገልፀዋል።

ከዚህ ውስጥ በክልሉ መክፈል ለማይችሉ 23 በመቶ ለሚሆኑ ወይም አንድ ሚሊዮን 329 ሺህ 183 አባወራዎች በማቀፍ ለማፍራት ታቅዷል ብለዋል።

በመሆኑም የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አገልግሎት በጤናው ላይ ያለውን ዘርፈብዙ ፋይዳ በመረዳት ማኅበረሰብ አባል መሆን ይገባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የተሠራውን እየጠበቅን ተጨማሪ ውብ ስፍራዎችን እንፍጠር!

ሰው እና አካባቢ፣ አንዳቸው የአንዳቸው ስሪትና ውጤቶች ናቸው። ሰው አካባቢውን ይሠራል፤ አካባቢ ደግሞ የሰው ልጆችን ይቀርጻል። እናም ሰው እና አካባቢ/ከባቢ አንዳቸው አንዳቸውን የሚገልጹ፤ አንዳቸው የአንዳቸው ሰብዕናና ልዕልና ማንጸሪያ ሆነው የሚታዩ ናቸው።

ምክንያቱም በዚህ ረገድ ሰው ውብ ስፍራዎችን በፈጠረና ባሰፋ ቁጥር፤ ለራሱና ለማኅበረሰቡ የአዕምሮ ዕረፍትን፣ የዕይታ አድማስን፣ የማንሰላሰያ ዓውድን ፈጠረ ማለት ነው። ይሄ ጉድኝት ደግሞ በሰው እና በተፈጥሮ/አካባቢ መካከል መልካም የሆነ መስተጋብርን በመፍጠር፤ የሰው ልጅ በኑሮው የተረጋጋ፣ ደስተኛ እና ብሩህ የሆነን ነገ የሚያልም እንዲሆን ያደርገዋል። ካልሆነው ሁነቱም፣ ውጤቱም በተቃራኒው ነው።

ይሄን መሰሉ እውነት የዓለም የዲፕሎማሲ ማዕከል፤ የአፍሪካ መዲና፣ የኢትዮጵያም መናገሻ ዋና ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ የትናንት እና የዛሬ እውነት ሆነው ይገለጻሉ። ምክንያቱም አዲስ አበባ ትናንት በጓዳ ጎድጓዳዋ እልፍ የቆሸሹ መንደሮችን ብቻ ሳይሆን፤ የቆሸሹ እና እጅጉን ለጤናም ጎጂ የሆኑ የተበከሉ ወንዞችን ታቅፋ ዓመታትን ዘልቃለች።

ይሄ ገጽታዋ ታዲያ ከተማዋን የማይመጥን ብቻ ሳይሆን፤ ነዋሪዎቿንም ለዘርፈ ብዙ (ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነልቦናዊና የጤና ጉዳዮችን ጨምሮ) ችግሮች ተዳርገው ቆይተዋል። የበዙት የከተማዋ ነዋሪዎችም በተጎሳቆሉ ቤቶችና መንደሮች ውስጥ፣ ከተባይ፣ ከዝናብ፣ ከጎርፍ፣ ከፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻዎች፣ አለፍ ሲልም ለሞት ከሚያጋልጡ ክስተቶች ጋር እንዲጋፈጡ ሆነው ኖረዋል።

አዲስ አበባ ከስምና ክብሯ በታች በሆነ ገጿ ስትገለጥ፤ ነዋሪዎቿም የከተሜነት ኑሮ ናፍቋቸው፤ ውብና ፅዱ ስፍራ የመኖር መብት እንዳላቸው እንኳን የሚያውቁ እስከማይመስል ድረስ በቆሻሻና ጢሻ ተውጠው ከርመዋል። ታዲያ ከተማዋን ከስምና ከግብሯ ያፋታ፤ ነዋሪዎቿንም ከሰብዓዊም፣ ከሞራላዊም ክብር ያናጠበ እውነት የሆነ ቦታ ላይ መገታት ነበረበት። እናም ከለውጡ ማግስት በተለይም በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሀሳብ አመንጪነት የተጀመሩት የከተማ ውበትና ፅዳት ሥራዎች፤ በኋላም የኮሪደር ልማት አስደማሚ ተግባራት መልስ በማግኘት ላይ ነው።

ምክንያቱም፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩን የበጎ ፈቃድ ተግባር ተከትሎ የተከናወኑ የተጎሳቆሉ መንደሮችን የማደስና የድሃ ቤቶችን የመሥራት ተግባር ሺዎችን የኑሮን ጣዕም እንዲያጣጥሙ ዕድል ሰጥቷል። በገበታ ለሸገር ፕሮጀክቶች ታግዞ የተከናወነው የአንድነት ፓርክ፣ የወዳጅነት አደባባይ፣ የእንጦጦ ፓርክ፣ የወንዝ ዳር ልማትና ሌሎችም የከተማዋን ነዋሪዎች የንጹሕና ውብ አካባቢዎችን ከፍ ያለ ፋይዳ እንዲረዱ፤ በስፍራዎቹም አረፍ ብለው የተሻለ ነገርን እንዲያስቡ ዕድል ፈጥረዋል።

ከዚህ በኋላ የተተገበረው የኮሪደር ልማት ተግባር ደግሞ፣ የከተማዋን ስምና ገጽ መግለጥ የቻለ፤ የነዋሪዎቿንም ሞራል የቀሰቀሰና የተሻለ ነገርን አብዝተው እንዲሹ ዕድል የሰጠ ሆነው። በዚህም ነዋሪው እንደ ቀድሞው ያረጁ ቤቶች ሲፈርሱ፤ የተበላሹ ስፍራዎች ሲዘምኑ፤ የተጎሳቆሉ መንደሮች ለተሻለ ልማት ሲታጩ፤… ቅሬታ እና ክስ ከማቅረብ ይልቅ በደስታ ተባባሪ ሆኖ መሳተፍ ችሏል።

በኮሪደር ልማት ሥራዎች የታየውም ይሄው ነው። መንግሥት የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ለመለወጥ ሲል የጀመረው የተቀደሰ ተግባር እንደመሆኑ፤ ነዋሪዎቹም ይሄንኑ በመገንዘብ የልማቱ መሳለጥ ተባባሪም፣ ንቁ ተሳታፊም በመሆናቸው ነው በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅጉን ከፍ ያለ ውጤት የታየበት ተግባራትን ማከናወን የተቻለው።

የኮሪደር ልማቱ ለአዲስ አበባ ስምና ግብር የሚመጥን ብቻ ሳይሆን፤ በልኳም እንድትገለጥ ያደረገ ነው። ለነዋሪዎቿም ውብ ከባቢን፣ ንጹሕን ስፍራን፣ ለዓይን ማራኪ እና ለልብም እረፍትን የሚያጎናጽፉ አከባቢዎችን የፈጠረ ነው። እነዚህ አካባቢዎች የፒያሳን ጎስቋላ መንደሮች አድሰዋል፤ ለአራት ኪሎ አካባቢም የውበት ካባን አጎናጽፏል፤ ለግንፍሌና ቀበና መስመሮችን ሞገስን ቸረዋል፤ ለሜክሲኮና ሣርቤት ሰፈሮችም አንጸባራቂ መልክ ለግሰዋል።

ይሄ ተግባር በእነዚህ ስፍራዎች ብቻ አልተዋሰኑም፤ ከሰሞኑም የቦሌ ኮሪደር ላይ ተጨማሪ ውበትና ግርማን ያላበሰ ተግባር ተፈጽሞ አዲስ አበባን በከፍታ፤ ነዋሪዎቿንም በደስታ አስተሳስሯል። በወቅቱ "የአፍሪካ፣ የኢትዮጵያና የአዲስ አበባ መግቢያ በር የሆነው የቦሌ መንገድ የኮሪደር ልማት ሥራችን ከተማችንን በሚመጥን ገጽታ ዘመናዊ መሠረተ ልማቶችን አካትቶ ሌላ ብስራት እና ተጨማሪ ድል ሆኖ ተጠናቋል፤" ሲሉ የከተማዋ ከንቲባ ባስተላለፉት መልዕክትም ይሄንኑ የሚያረጋግጥ ነው።

እነዚህ የኮሪደር ልማት መስመሮች ሰፊ የመኪና፣ የእግረኛ እና የብስክሌት መንገድ፤ የመኪና ማቆሚያ ፓርኪንጎች፣ የታክሲ እና አውቶቡስ መጫኛ/ማውረጃዎች፣ የሕዝብ መናፈሻዎች፣ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ፏፏቴዎች፣ የሕዝብ መፀዳጃ ስፍራዎች እንዲሁም የከተማዋን ፕላን የጠበቀ የቀለምና የመብራት ሥራን አካትተው፤ እጅግ በተዋበ መንገድም ገንብተን ለሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገው ለሕዝቡ የተበረከቱ ናቸው።

ይሁን እንጂ እነዚህ ውብ ሆነው ለሕዝቡ የተበረከቱ የልማት ውጤቶችና ውብ ስፍራዎች ለሚፈለገው ዓላማ ይውሉ ዘንድን ከፍ ያለ ጥበቃን የሚሹ ናቸው። በመሆኑም እንዲህ ውብ ተደርጎ የተገነባውን መሠረተ ልማት መላው የከተማዋ ነዋሪ ከፀጥታ አካላት ጋር በመሆን በባለቤትነት መንፈስ ሊንከባከብ እና ሊጠብቃቸው፤ ከዚህ ጎን ለጎንም የሚመጥኑትን ሌሎች ውብና ፅዱ ከባቢዎችን በመገንባት ሂደት የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ስፖሊሲው ውጤታማነት በይቻላል መንፈስ የተቃኘ የተሻለ አስተሳሰብ ያስፈልጋል

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

የሀገራችን ኢኮኖሚ ስብራት ዓመታትን ያስቆጠረ፣ ሀገር እና ሕዝብን ብዙ ዋጋ ሲያስከፍል የቆየ ስለመሆኑ ብዙም ለሰሚ አዲስ አይደለም። ችግሩን ለመፍታት የለውጥ ኃይሉ ወደ ሥልጣን ከመጣ ማግስት ጀምሮ ሰፊ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ በማዘጋጀትም ወደ ሥራ ገብቷል።

ፖሊሲው ላለፉት ስድስት ዓመታት ተስፋ ሰጭ ውጤቶችን ማስመዝገብ የቻለ፣ ሀገር ገብታበት ከነበረው አጣብቂኝ እንድትወጣ ጥልቅ አቅም የፈጠረ ነው። የሀገሪቱ ኢኮኖሚም በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖም በየዓመቱ እድገት እንዲያሳይ ረድቷል። ይህም ፖሊሲው በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ አስችሏል ።

ሰሞኑን እንደ ሀገር ተግባራዊ እየሆነ ያለው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያም የዚሁ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው። ማሻሻያው አጠቃላይ ሀገራዊ ኢኮኖሚውን ሊብራላይዝድ ለማድረግ እየተደረገ ያለው ጥረት አንድ አካል ነው። የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ገበያ መር እንዲሆን ወሳኝ ድርሻ ያለው ነው። በኢኮኖሚ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የቆየውን የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋትና መዛባት ለማሻሻልም ይረዳል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አካል የሆነው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሐ ግብር ላይ የተመሠረተና በቀጣይ ሥራ ላይ ከሚውሉ ሰፊ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች መካከል አንዱ ነው። ዋና ግቡ ቀጣይነት ያለው፣ መሠረተ ሰፊና ሁሉን አሳታፊ የኢኮኖሚ ዕድገት መኖሩን ማረጋገጥ ነው።

ሀገራት የኢኮኖሚ ችግር ውስጥ ሲገቡ የተለያዩ ማሻሻያዎችን ማድረግ የተለመደ ነው። በዚህ ውስጥም በርካታ ያለፉ ሀገራት መሆናቸው ይታወቃል። ለአብነትም ሕንድ፣ ቻይና፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ብራዚል በተለያዩ ወቅቶች የሪፎርም እና በማክሮ ኢኮኖሚው ላይ ማሻሻያ በማድረግ ችግሮቻቸውን ለማለፍ ችለዋል። በተለይም የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመፍታት በርካታ ሀገራት አያሌ ምክረ ሃሳቦችን ተግብረዋል። በዚያው ልክ ደግሞ የምዕራባውያን የምጣኔ ሀብት ፍልስፍና እንደ ወረደ ለመተግበር ሞክረው ለከፍተኛ ኪሳራ የተዳረጉ ሀገራትም አሉ።

በኢትዮጵያም የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ማድረግ ተገቢ እና ወቅቱ የሚጠይቀው ቢሆንም አተገባበሩ ግን እጅግ ከፍተኛ ጥንቃቄ፣ እውቀት እና ብስለትን የሚጠይቅ ነው። ኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት ያለፈችባቸውን ችግሮች በማቃለል አስተማማኝ ዘላቂ ልማት ማምጣት የሚያስችል፤ የሁሉንም ዜጋ ልዩ ትኩረት የሚጠይቅ ነው።

> ኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት ያለፈችባቸውን ችግሮች በማቃለል አስተማማኝ ዘላቂ ልማት ማምጣት የሚያስችል፤ የሁሉንም ዜጋ ልዩ ትኩረት የሚጠይቅ ነው

መንግሥት እንደገለፀው፤ የማሻሻያ እርምጃዎቹ በመደረጋቸው ምክንያት፤ ‹‹በሚቀጥሉት አራት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ ስምንት በመቶ ያህል ያድጋል፤ የዋጋ ንረት ወደ 10 በመቶ የተጠጋ ይሆናል። የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 11 በመቶ ይደርሳል፣ የመንግሥት ዕዳ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ወደ 35 በመቶ ዝቅ ይላል።

የወጪና የገቢ ንግድ ዋጋ ወደ 20 ቢሊዮን ዶላር ያድጋል፤ ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ወደ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ከፍ ይላል፤ ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ክምችት ከ10 ቢሊዮን ዶላር (የ3.3 ወራት የገቢ ሸቀጦችን ወጪ ለመሸፈን የሚበቃ) በላይ ይሆናል››። እነዚህ ትንበያዎች በቀጣይ ዓመታት ከላይ በተጠቀሱት ማሻሻያዎች ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን የኢኮኖሚ ሽግግር ደረጃ የሚያመለክቱ ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱትን ለውጦችን ማምጣት ብዙ ሥራ የሚጠይቅ ነው። ከተለመደው አሠራርና አስተሳሰብ ወጥቶ መንቀሳቀስን ይጠይቃል። በተለይም የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት እና የተቋማቱ አመራሮች ጉዳዩ ሀገርን የማሻገር ጥልቅ ታሪካዊ ጉዳይ መሆኑን በአግባቡ ተገንዝበው በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።

ላለፉት በርካታ ዓመታት የነበረው የንግድ ሚዛን መዛባት ለማስተካከል የሀገር ውስጥ ምርትን በብዙ እጥፍ ማሳደግ ፣ ዘመናዊ ቴክሎጂዎችን፣ ሳይንሳዊ አሠራሮችን፣ ምሑራዊ ምክሮችንና እይታዎችን በመተንተን ወደ ተግባር መቀየር ይኖርባቸዋል። ወጣቶችም ሥራ ጠባቂ ከመሆን ወደ ሥራ ፈጣሪ የሚሸጋገሩበት ዕድል ማመቻቸትም ያስፈልጋል።

እንደ ሀገር በኮንትሮባንድ ንግድ ላይ ጠንካራ አቋም መያዝና ማስተካከል እጅጉን ወሳኝ ነው። ከባንክና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ውጭ የሚንቀሳቀሰውን ገንዘብ ወደ መደበኛ ሥርዓት ማስገባት፤ ከሁሉም በላይ አስተማማኝ ሠላም ማስፈን ያስፈልጋል።

ከውጭ የሚገቡ በርካታ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ተኪ ምርቶች ቦታ ሊለቁ ይገባል። ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሙ እያመጣ ያለውን ውጤት በየወቅቱ መገምገም፤ የተጀመሩ ሜጋ ፕሮጀክቶችን በፍጥነት በማጠናቀቅ ትርፋማ ወደሚሆኑበት ሁኔታ ማሸጋገር፣ የሀገሪቱን ትልቁን ሀብት የተሸከሙትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የማምረትና አገልግሎት የመስጠት አቅማቸው አሁን ካሉበት ሁኔታ እጅግ የላቀ አፈፃፀም እንዲኖራቸው መትጋት መሥራት ይገባል።

በአጠቃላይ ሀገሪቱ ከገጠማት የማክሮ ኢኮኖሚ ሕመም ሙሉ ለሙሉ ለማገገምና የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ውጤታማ ለማድረግ ከመጣንበት መንገድ ላቅ ባለ ሁኔታ በይቻላል መንፈስ የተቃኘ የተሻለ አስተሳሰብ ያስፈልገናል። ምሑራን በእውቀታቸው፣ ባለሃብቶች በገንዘባቸው፣ ፖለቲከኞች በሐሳባቸው እንዲሁም በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ አካላት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ራሳቸውን ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ።

# ታዳጊ ሀገራት ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

ግቦች ጋር የተያያዘ መሆኑን ያወሱት ዳይሬክተሯ፤ ስምምነቱን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን ተናግረዋል።

እንደ ሻሪ ስፒገል ገለጻ፤ ከአፍሪካ ሀገራት በተጨማሪ ሌሎችም በችግር ውስጥ በመሆናቸው መርሐግብሩን በማሳካት ረገድ ክፍተቶች ይታያሉ። የዓለም አቀፉ መዋቅርም ለታዳጊ ሀገራት አስቸጋሪ በመሆኑ በጉዳይ ዙሪያ ውይይት እየተደረገበት ይገኛል።

በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ያለውን የዘላቂ ልማት ግቦች ዕቅድ ለማሳካት በዓመት 4 ትሪሊዮን ዶላር የፋይናንስ ክፍተት አለ ያሉት ዳይሬክተሯ፤ የኮቪድ ተፅዕኖ፣ የራሺያና ዩክሬን ጦርነት፣ የአየር ንብረት ለውጥና በዓለም አቀፍ ዙሪያ የተከሰቱ ቀውሶች የዘላቂ ልማት ግቦችንና የአዲስ አበባን አክሽን አጀንዳ ለማሳካት እየተደረገ ያለውን ጥረት ከባድ ማድረጋቸውን ጠቁመዋል።

ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም በቂ አይደለም ያሉት ሻሪ ስፒገል፤ የኮቪድ ቀውስ በዓለምአቀፍ የፋይናንስ ሥርዓት ውስጥ ያሉትን ክፍተቶች አጉልቶ ማሳየቱን አውስተዋል።

በአራተኛው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ልማት ቅድመ ጉባኤ ኮንፍረንስ ሁሉም ሀገራት በሚባል መልኩ የአዲስ አበባ አክሽን አጀንዳ እንዲሳካ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ እንደሆኑ በመግለጽ ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

አተገባበሩ ያለበትን ደረጃ በመገምገም በቀጣይም መደረግ ስላለባቸው ጉዳዮች ዙሪያ አዳዲስ ሀሳቦችን ማቅረብ መጀመራቸውንም አክለዋል።

ዳይሬክተሯ ሰሞኑን በአዲስ አበባ የተደረገው ኮንፍረንስ የመንግሥትን ፋይናንስ ዘርፍ ከግሉ ጋር እንዴት አጣጥሞ መጠቀም እንደሚቻልና በዘላቂ የልማት ግቦች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ምን መደረግ እንዳለበት ሀገራት የተሻለ ግንዛቤ እንዲይዙ የሚያደርግ መሆኑን ገልጸዋል።

# በወለድ ተመን ላይ የተመሠረተው ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

ብሔራዊ ባንክም በማክሮ ኢኮኖሚና በባንክ ዘርፉ የታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ይህንን የፖሊሲ ማሻሻያ ትግበራ መጀመሩን አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም በማሻሻያው የተካተተውና ብሔራዊ ባንኩ እከተለዋለሁ ያለው በወለድ ተመን ላይ ላይ የተመሠረተ የገንዘብ ፖሊሲ ሲባል ምን ማለት ነው? ኢኮኖሚው ላይ ምን አይነት ለውጦችን ያመጣል? ምንስ ጥቅም ይኖረዋል? በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ ከኢኮኖሚ ባለሙያዎች ጋር ተወያይቷል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን የሰጡት የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህር ዘመዴ ጫሚሶ እንደገለጹት ብሔራዊ ባንክ ከዚህ ቀደም ከነበረው በገንዘብ አቅርቦት ላይ የተመሠረተ ፖሊሲ ወደ በወለድ መጠን የሚመራ የገንዘብ ሥርዓት መሻገሩ ባንኩ የብሔራዊ ባንክ ሚናን እንዲወጣ የሚያደርገው ነው ።

በዚህ ፖሊሲም ብሔራዊ ባንክ በገበያ ውስጥ የሚኖርን የገንዘብ አቅርቦት ለመወሰን አቅም የሚያገኝ ሲሆን በገበያው ውስጥ በመጋጋል እንዲሁም በመቀዛቀዝ ምክንያት የሚመጣን የዋጋ ንረት የገንዘብ ዝውውሩ እንደ አመቺነቱ በመግታትና በመልቀቅ የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር ከበፊቱ በተሻለ ምቹ ሜዳን ያገኛል ይላሉ።

አቶ ዘመዴ ፖሊሲው በዚህ የሚመራ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ግን ብሔራዊ ባንክ ይህንን የማድረግ አቅም ይኖረዋል ብለው እንደማያስቡና በሂደት ግን ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

ለዚህም በአሁኑ ጊዜ የኑሮ ውድነት እንዳይከሰት መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ከተለያዩ አካላት እያገኘው ያለውን የገንዘብ ድጋፍ ለዋጋ ንረት ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የመደጎም



ሥራውን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለዋል።

ሌላኛው ያስቀመጡት የመፍትሔ አቅጣጫ መንግሥት ሞኒታሪና ፊስካል ፖሊሲውን አጣምሮ በመሥራት ለአጭር ጊዜም ቢሆን ከውጭ የሚገቡ መሠረታዊ እቃዎች ላይ የሚጥለውን ቀረጥ በመቀነስ የኑሮ ውድነቱን መከላከል እንደሚቻል መክረዋል።

ይህ የገንዘብ ፖሊሲም የብድር አቅርቦት ላይ የወለድ መጠኑ በአቅርቦትና በፍላጎት ላይ የሚመሠረት የሚያደርግ ሲሆን ይህም አጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓቱን በማዘመን ገበያው እራሱን በራሱ የሚመራ ስለሚያደርግ በብሔራዊ ባንክ ላይ የሚኖረውን ጫና እንደሚቀንስ አብራርተዋል።

ሌላኛው በዚህ ፖሊሲ ላይ ሀሳባቸውን ለኢፕድ ያጋሩት የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ቆስጠንጢኖስ በርሄ ተስፋ (ዶ/ር) እንደገለጹት አዲሱ የብሔራዊ ባንክ መዋለ ንዋይ ፖሊሲ ኢኮኖሚው ላይ ያለውን የገንዘብ ፍሰት ያለውን ተፅዕኖ ለመቆጣጠር ወለድን ይጠቀማል።

ማዕከላዊ ባንክ ኢኮኖሚው በሚቀዘቅዝበት ጊዜ ያለውን ወለድ በጣም ዝቅተኛ በማድረግ ሰው እንዲበደር የሚያበረታታ ሲሆን ኢኮኖሚው ደግሞ በጣም ተነቃቅቶ ወደ ዋጋ ግሽበት ሲሄድ የወለድ መጠንን ከፍ በማድረግ የገንዘብ ዝውውሩን የመግታትና የኑሮ ውድነቱን መቆጣጠር ያስችለዋል።

በአሁኑ ሰዓት ብሔራዊ ባንክ ባንኮች እርስ በራሳቸው የሚበዳደሩበት የወለድ መጠን 15 በመቶ ያደረገ ሲሆን ባንኮች ለደንበኞቻቸው የሚያበድሩበት የወለድ መጠን ግን ራሳቸው ይወስናሉ።

ይህም ብሔራዊ ባንክ የገንዘብ ፍሰቱ እንዲቀንስ በማድረግ የዋጋ ንረቱ ለመቆጣጠር ያግዛል ያሉ ሲሆን ለአብነትም በአሁኑ ሰዓት የዋጋ ንረቱ ከ30 በመቶ ወደ 19 በመቶ የወረደው ዋነኛ ምክንያቱ የገንዘብ ፍሰቱ በመቀነሱ መሆኑን ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) ያነሳሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ይሄ የመዋለ ንዋይ ፖሊሲ ኢንቨስትመንቱን ያነቃቃል ያሉ ሲሆን ይህ ግን እንደ ሠላም ጉዳዮችና የጥቁር ገበያን መቆጣጠር ሲቻል መሆኑን አንስተዋል።

# ማሻሻያው ድሃ ተኮር ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

በፖለቲካውና በማኅበራዊው ዘርፉ እንደወሰደው የሪፎርም እርምጃዎች ሁሉ ኢኮኖሚውን ከቀውስ ለመታደግ ዘላቂ ዕድገትን ለማስቀጠል የኢኮኖሚ ሪፎርም አስፈላጊ ነበረ። የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ችግር ውስብስብና መፍትሔውም ዘርፈ ብዙ ምሉዕ እይታ የሚፈልግ ነው" ይላል የፕላንና ልማት ኮሚሽን ሚያዚያ 2013 ዓ.ም ያዘጋጀው "የኢኮኖሚ ማሻሻያ መነሻዎች፣ የተከናወኑ ተግባራት እና የተገኙ ውጤቶች" ሰነድ።

ሰነዱ እንደሚያትተው ኢኮኖሚው ያጋጠሙትን ማነቆዎች በዘላቂነት ለመቅረፍና የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማስቀጠል የማክሮ ኢኮኖሚ፣ የዘርፎችና የመዋቅራዊ ማሻሻያዎች ላይ የሚያተኩረው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ተነድፈው እየተተገበሩ ይገኛሉ። እነዚህ ማሻሻያዎች የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ በመፍጠር፣ ለዘርፎች ምርታማነትና ቅልጥፍና ትኩረት በመስጠት፣ እንዲሁም በመዋቅራዊ ችግሮች መፍትሔ በመሻት የኢኮኖሚ ዕድገቱን በማስቀጠል ያለሙ ናቸው።

በዚህም በዋናነት የሀገር ውስጥ ገቢንና የሸማቹን አቅም በማሳደግ የምግብ ዋስትናን በማሻሻል፣ የሥራ ፈጠራ አቅምንና የሥራ ዕድልን በማሳደግ ሥራ አጥነትን ትርጉም ባላው መልኩ ለመቀነስ፣ የማምረት አቅም አጠቃቀምንና የግብዓት አቅርቦትን በማሳደግ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል፣ የሸቀጦች ዋጋን በማረጋጋት፣ የዲጂታል ኢኮኖሚ አቅም ግንባታና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ የግሉ ዘርፍ ሚናን በማጎልበት፣ የውጪ ንግድን በማሳደግና የገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካትና የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ በዚህም የውጭ ዕዳ ጫናን ለመቀነስ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ዋና ዋና ዓላማዎች ነበሩ።

የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ማድረግ ካስፈለገባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ ተፈጥሮ የነበረው ከፍተኛ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ሲሆን፤ ይህንንም በማስተካከል በተለይም የማክሮ-ፋይናንሺያል ማሻሻያዎች ተለይተው በትኩረት ሲሠራባቸው ቆይተዋል። እነዚህ የማክሮ-ፋይናንሺያል ማሻሻያዎች ሲወሰዱ የቆዩት የማክሮ ኢኮኖሚ ምኅዳሩን በማሻሻል በተለይም የማረጋጋት የዋጋ ሁኔታ፣ የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመን፣ የተቃለለ የውጭ ዕዳ ጫና፣ እንዲሁም ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲኖር ለማድረግ የታቀደ ነበር። እነዚህንም ዋና ዋና ዓላማዎች በማሳካት በርካታ የገንዘብ ፖሊሲ እና የፊሲካል ፖሊሲ ማሻሻያዎች እንዲሁም የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የኢኮኖሚ ዕድገትና የውጭ ዘርፍ አፈጻጸም፣ እና የፋይናንስ ዘርፍ ልማትና የፋይናንስ አካታችነት ማሻሻያ እርምጃዎች ተወስደዋል።

በዚህ ዙሪያ ሲወሰዱ ከነበሩት ተግባራት መካከል አንዱ የገንዘብ ፖሊሲውን ማሻሻል ነው። እስከ አሁን ሲወሰዱ የቆዩት የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ እርምጃዎች ኢኮኖሚውን ከነበረበት የቁልቁለት ጉዞ በመታደግ እና በማነቃቃት ከፍተኛ ውጤት አምጥተዋል። የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ የትግበራ ጊዜያት ካጋጠሙ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ተግዳሮቶች አንፃር ሲታይ ሲወሰዱ የቆዩት እርምጃዎች ከሞላ ጎደል ውጤታማ ነበሩ ማለት እንደሚቻል በሰነዱ ተቀምጧል።

በፕላንና ልማት ሚኒስቴር የልማት እቅድና የመንግሥት ኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥራ ክፍል ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ በረከት ፍስሐ ፅዮን የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማቃናት ከተወሰዱ ርምጃዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይፋ የተደረገውን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ለዜጎች የሚሰጠው ፋይዳ አስመልክተው እንደሚያብራሩት፤ በማሻሻያው ለመንግሥት ሠራተኞች የኑሮ ውድነት መደጎሚያ ደመወዝ ለመጨመር፤ በሕዝቡ በተለይም አነስተኛ ገቢ ባላቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማቃለል መንግሥት ከውጭ የሚገቡ የአንዳንድ መሠረታዊ ሸቀጦችን ዋጋ በጊዜያዊነት ለመደጎም ወስኗል።

ማሻሻያው ሲደረግ ጥልቅ በመሆኑ ተፅዕኖ ይደርስባቸዋል ተብለው የታሰቡ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ለመታደግ ብዙ ተሠርቷል የሚሉት አቶ በረከት፤ ይህ የድርድር አካል ሆኖ ዝግጅት ተደርጎበት እንደቆየ ይናገራሉ። በዚህም ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞችን ተደራሽ የማድረግ፤ መሠረታዊ የሆኑ እንደ ነዳጅ፤ ማዳበሪያ፤ ዘይት መድኃኒት ያሉ ምርቶች ድጎማ እንደሚደረግባቸው አመላክተዋል።

እንደ አቶ በረከት ገለጻ፤ ለዚህ የሚሆን በቂ ፋይናንስም የተዘጋጀ ሲሆን፤ በተጨማሪ መንግሥት የገቢ አቅምን በማሳደግ ተፅዕኖ የሚደርስባቸውን ዜጎች ለመታደግ በየወቅቱ የሚሠራቸው በርካታ ሥራዎች ይኖራሉ። ይህም ማሻሻያውን ተከትሎ በገበያ ውስጥ የሚፈጠረውን የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር የሚያስችል ይሆናል።

ይህም ሆኖ እንዲህ አይነት ትልልቅ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ሲወሰዱ በገበያ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮች እንደሚኖሩ ይጠበቃል ብለዋል አቶ በረከት። ለዚህም በመንግሥት በኩል ማኅበረሰቡ ለችግር እንዳይጋለጥ መሠረታዊ በሚባሉ ሸቀጦች ላይ የሚወሰዱ ተከታታይነት ያላቸው ቁጥጥሮችና እርምጃዎች እንደሚኖሩ በማብራሪያቸው ጠቅሰዋል። በተለይም ከጉዳዩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የማይኖራቸው የዋጋ ጭማሪዎች ላይ ጥብቅ ክትትል የሚደረግ ይሆናል ነው ያሉት።

"እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ማሻሻያው የተደረገው እንደ ከዚህ ቀደሙ የውጪ ምንዛሪ መጠንን ማዳከም ሳይሆን ገበያን መሠረት ያደረገ የውጪ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት መዘርጋት ነው። ይህም ማለት መንግሥት ዋጋ የሚተምንበት ሳይሆን ባንኮችና ደንበኞች በሚኖራቸው ግንኙነት የሚፈጠር የዋጋ ተመን ይኖራል ማለት ነው። ይህም ከነበረው ከተለመደው አካሄድ የተለየ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። በዚህም ከውጪ የሚገቡ ምርቶች በተወሰነ ደረጃ የዋጋ ጭማሪ ሊያሳዩ ይችላሉ" ሲሉ ይገልጻሉ።

እንደ አቶ በረከት ማብራሪያ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከውጪ የሚገቡትን ምርቶች ምንነት ተለይቶ መታየት አለበት። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ከከተሞች ውጪ የሚኖር ነው። የፍጆታው አይነትም በቀዳሚነት ራሱ የሚያመርታቸው ሲሆኑ አንዳንድ በግብዓትነት የሚጠቀምባቸውም በስትራቴጂ የተያዙት ናቸው። በመሆኑም ይከሰታል ተብሎ የሚጠበቀው ጭማሪ አብዛኛውን ዜጋ ለተጋነነ ችግር የሚያጋልጥ አይሆንም። ከዚህም በተጨማሪ አብዛኛው ሕዝብ እንደ ትምህርት ጤና ያሉ መሠረታዊ ነገሮችን በነፃ ተጠቃሚ መሆኑ ማሻሻያውን ተከትሎ ለሚፈጠር ለውጥ የመጋለጥ ዕድሉም ዝቅተኛ ነው። ይህም ሆኖ አብዛኛውን ሕዝብ የሚነኩ ጉዳዮችና ያንን ተከትሎ የሚከሰቱ ነገሮችን ለመቆጣጠር ዝግጅት ተደርጓል። በአንጻሩ ይፈጠራል ተብሎ የተሰጋው የአንዳንድ ምርቶች ዋጋ መጨመር የሀገር ውስጥ አምራቾችን የሚያበረታታ ይሆናል።

የፐብሊክ ፖሊሲና ምጣኔ ሀብት ምሑሩ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ በጥቁር ገበያ ላይ የተሰማሩ አካላት ለአጭር ጊዜ ኢኮኖሚው ላይ ትርምስ ለመፍጠር ቢሞክሩም፤ ፖሊሲው የሀገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ ላይ ትኩረት የሚሰጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሕዝቡ በከፍተኛ ደረጃ ወደ ሥራ እንዲሰማራና ገቢውን እንዲያሳድግ የሚያግዝ ነው ብለዋል።

የግል ሴክተሩን እያደገ በመሄድበት ጊዜም ቋሚ ገቢ ያላቸው የመንግሥት ሠራተኞች በስፋት ወደ ግሉ ዘርፍ የመዞር ዕድሉ ስላላቸው ይህ አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ለውጥ ሚናው ትልቅ እንደሆነ ጠቅሰዋል። የማሻሻያ ፖሊሲውን ተግባራዊ ማድረጉ ላይ ግን ልዩ ትኩረት መደረግ እንዳለበት ይመክራሉ። ይህ አይነት ፖሊሲ እንደነ ቻይና ያሉት ሀገራት እንደሚጠቀሙበት ጠቅሰው፤ ይህ በኢትዮጵያ ተግባራዊ መደረጉ ከሀገር ውስጥ ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያጋጠመውን የኢኮኖሚ ቀውስ ተከትሎ ያጋጠመውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍና ዘላቂ ኢኮኖሚ ለመገንባት ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያውን አስመልክቶ በዝርዝር በወጣው መረጃ፤ በሚቀጥሉት ሳምንታትና ወራት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታን የማረጋገጥ ቁልፍ ኃላፊነቱን ከመወጣት ጎን ለጎን የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያውን ስኬታማና ውጤታማ በማድረግ ላይ የሚያተኩር ይሆናል።

በማሻሻያ እርምጃዎቹ ምክንያት በሚቀጥሉት አራት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ በስምንት በመቶ እንደሚያድግ፤ የዋጋ ንረት ወደ 10 በመቶ እንደሚወርድ፣ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 11 በመቶ እንደሚደርስ፣ የመንግሥት ዕዳ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ወደ 35 በመቶ ዝቅ እንደሚልና የወጪና የገቢ ንግድ ዋጋ ወደ 20 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያድግ ባንኩ በትንበያው አስቀምጧል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የአፈር አሲዳማነትን የማከም ሥራዎችና የታየ ለውጥ

**ማህሌት አብዱል**

ለሰው ልጆች ከሚያስፈልጉት ዋና እና መሰረታዊ ነገሮች አንዱ አፈር ነው። የዘርፉ ተመራማሪዎች እንደሚሉትም፤ አፈር የሰውም ሆነ የእንስሳት ምግብ የሚጀመርበት ከመሆኑም ባሻገር ያለአፈር ህልውናን ማስቀጠል አዳጋች ነው። ይህ የተፈጥሮ ሃብት በምድር ለሚበቅሉት አዝርዕት ሁሉ መብቀያ፣ ለፍጥረታት ምግብ መገኛ መሆኑን በሚገባ በመገንዘብ ዋጋ ሰጥቶ ደህንነቱን ማስጠበቅ ላይ የተከናወነው ተግባር እምብዛም እንደሆነ እሙን ነው።

አፈር በተለያዩ ምክንያቶች ደህንነቱ ለአደጋ ካለበት ሁኔታ መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው። በመሬት መሸርሸር፣ በንፋስና በመሳሰሉት ተጠርጎ እየተወሰደ ያለበት ሁኔታም ለእዚህ ሌላው ማሳያ ነው።

የአፈር ኢሲዳማነት ደግሞ ሌላው ችግር ሆኗል። በሀገራችን አፈርን ከአሲዳማነት መታደግ ባለመቻሉ ሳቢያ ሊታረስ እና ሰብል ሊያበቅል የሚችለው ውስን የመሬት ክፍል ለከፍተኛ ጉዳት ሲዳረግ ይታያል።

ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ያገኘነው መረጃ እንደሚያሳየውም፤ ግማሽ የሚሆነው የዓለም ክፍል አፈር በአሲዳማነት የተጠቃ ነው። በተለይም እስያ፣ መካከለኛው አፍሪካ፣ ሰሜን አሜሪካና ደቡብ አሜሪካ እንዲሁም አውስትራሊያ በአፈር አሲዳማነት ተጠቅተዋል። በዚህ ችግር የተነሳ ሊታረስ የሚችለው 32 በመቶው መሬት ብቻ ሲሆን፣ የህዝብ ቁጥር እድገት በከፍተኛ ደረጃ በሚጨምርባቸው አካባቢዎች ላይ የአሲዳማነት መጠኑ የከፋ እየሆነ በመምጣቱ ችግሩን አሳሳቢ አድርጎታል።

የግብርና ሚኒስቴር መረጃ እንዳመለከተው፤ ወደ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር ወይንም አሁን ከሚታረሰው መሬት 43 ከመቶው በአሲዲቲ እየተጠቃ ነው። ሶስት ሚሊዮን ሄክታሩ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ በአሲዲቲ ተጠቅቷል። በዚህ መሬት ላይ ማዳበሪያም መጠቀም ቢቻል በቂ ምርት ሊገኝበት አይችልም።

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የምርምር ማዕከላት ዳይሬክተርና የአሲዳማ አፈር ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር ገረመው ታዬ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያም የአፈር አሲዳማነት በስፋት የሚታየው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ባለባቸውና የምግብ እጥረት በሚታይባቸው አካባቢዎች ነው። በሌላ መረጃ እንደተመለከተው ደግሞ ስርጭቱ ደግሞ ከሰሜን ምዕራብ፤ ከመካከለኛው ወደ ምዕራብና ከደቡብ ምዕራብ ወደ ምዕራብ ሲኬድ የአሲዳማ አፈር ጫና እየጨመረ ይሄዳል። የምስራቁ ክፍል የአፈር አሲዳማነት እምብዛም አይታይበትም።

‹‹ከመካከለኛው ወደ ምዕራቡ የሃገራችን ክፍል በተጓዝን ቁጥር የአሲዳማነት መጨመር በከፍተኛ ሁኔታ ይታያል፤ ከዚህ ውስጥ 28 በመቶው በጣም ጠንካራ አሲድ ያለበት ሲሆን፣ 13 ነጥብ ሁለት በመቶው ደግሞ በጣም በከፍተኛ ደረጃ አሲዳማ ሆኖ የኮምጣጣነት መጠኑም ወደ አራት ነጥብ አምስት የሚጠጋ ነው›› በማለት ዶክተር ገረመው ያብራራሉ።

አሲዳማነትን በኢትዮጵያ የከፋ የሚያደርገውም 88 በመቶ የሚሆነው ህዝብ የሚኖርበት አካባቢ አፈር አሲዳማ መሆኑ ነው የሚሉት ዶክተር ገረመው፤ በተጨማሪም 86 በመቶ የሚሆነው የእንስሳት ሃብት የሚገኝበት አካባቢም በተመሳሳይ መልኩ ችግሩ ጎልቶ እንደሚታይበት ያመለክታሉ።

እንደ ከፍተኛ ተመራማሪው ማብራሪያ፤ አሲዳማነት ያለው አፈር በተለይ ለሰብሎች እድገት ጠንቅ ነው። አሲዳማነት እየተስፋፋ በመጣ ቁጥር ደግሞ ከዚህ ቀደም ይታረስ የነበረው መሬት ሳይቀር ምርታማነቱ እየቀጨጨ ይመጣል፤ አለፍ ሲልም ምንም አይነት ምርት እስካለመስጠት ሊደርስ ይችላል። በተለይም አሲዳማነት ባለባቸው አፈሮች



ዶክተር ገረመው ታዬ

ላይ የሃይድሮጂን ክምችት ከፍተኛ ነው፤ በዚህም ጎጂ የሆነ የአልሙኒየም ንጥረ ነገር በስፋት ይገኛል።

‹‹ይህ አልሙኒየም ደግሞ በአፈር ውስጥ ተከማችቶ መገኘት ለሰብሎች ስር እድገት አደገኛ ነው። እንደፀጉር የቀጠኑ ስሮችን ሳይቀር ያቃጥላል፤ ይገላል›› ሲሉ ያስረዳሉ። በእነዚህ አካባቢዎች ሰብሎች ውሃም ሆነ በቂ ምግብ ቢያገኙም በየጊዜው እየተዳከሙ እንደሚሄዱ ጠቁመው፤ በተቃራኒው ደግሞ አረሞች የሰብሎችን ምግብ በመሻማት የሚፋፉበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ያመለክታሉ።

እንደ ዶክተር ገረመው ማብራሪያ፤ በተፈጥሮ ከሚከሰተው የአፈር አሲዳማነት በተጨማሪ የአካባቢው የዝናብና የአየር ሙቀትና ቅዝቃዜ መዛባት የራሱ አስተዋፅኦ አለው። በተለይም ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያለባቸው አካባቢዎች የአሲዳማነት ችግር ጎልቶ ይታይባቸዋል። በቆላማና ደረቅ በሆኑ አካባቢዎች የአሲዳማነት ችግር የለም። በመሆኑም የአፈር ውስጥ የዝናብ መጠን መቆጣጠር አዳጋች በመሆኑ የበለጠ ተመራጭ የሚሆነው እንደየአካባቢው የአየር ንብረት ተስማሚ የሆኑ ሰብሎችን ማብቀል ነው።

ከዝናቡ ጋር ተያይዞም ሞቅ ያለ አየር በዝናብ ሲታጀብ ብረት የሆኑ ካልሺየም፣ ፖታሺየም፣ ማግኒዚየም የሚባሉት ንጥረ ምግቦች በቀላሉ በአፈር ውስጥ ሊገቡ ስለሚችሉ ዝናብ ሲጥል ወደ ውስጥ የመስረግና ከሰብሎች የስር እድገት በታች በጣም ርቀው ስለሚሄዱ ለመጠቀም እንደሚያስቸግር ያስረዳሉ። በተቃራኒው ደግሞ በአየር ሙቀትና ቅዝቃዜ እንዲሁም በዝናብ መብዛት ምክንያት እንደ ናይትሮጂን አዮን የሚባሉት መርዛማ የሆኑ ንጥረ ነገሮች ወደላይኛው የመሬት ክፍል ስለሚቀሩ ለሰብሎች ስር እድገት አስቸጋሪ ይሆናል ሲሉ ያመለክታሉ።

የሰው ልጆችም ለአፈር አሲዳማነት መስፋፋት የራሳቸው አስተዋፅኦ እንዳላቸው ዶክተር ገረመው ይናገራሉ። አብነት አድርገውም ‹‹ብዙውን ጊዜ በምርት ስብሰባ ወቅት የምንመገባቸውን ለይተን ተረፈ ምርቱን ወይም ቃርሚያውን፣ የስንዴ፣ የበቆሎ፣ ገለባና ጭድ እዛው አፈር ላይ መተው ሲጠበቅብን ምንም ሳናስቀር የምናጭደው በመሆኑ የአፈሩን ለምነት የሚጨምሩ ነገሮች እንዲሟጠጡና አሲዳማነት እንዲስፋፋ እናደርጋለን›› ይላሉ። ተረፈ ምርቱ ተመልሶ በአፈሩ ለምነት ላይ አስተዋጽኦ ማድረግ ሲገባው የሚሰበሰብ በመሆኑ የአፈርን ካርቦን ከመጨመር ይልቅ የሰብል ንጥረ ነገር የሚሳሳበት ሁኔታ ይከሰታል። በተጨማሪም የካርቦን ምጣኔ በአፈር ውስጥ ስለሚዛባ አሲዳማነት እየተስፋፋ ይሄዳል ሲሉ ያብራራሉ።

በመሆኑም አርሶአደሩ ሰብሉን ከነስሩ ነቅሎ ከመውሰድ ይልቅ የተወሰነውን ማሳ ላይ በመተውና ከአፈር ጋር በመደባለቅ የአፈርን ምርታማነት መጨመር እንደሚገባው ያስገነዝባሉ።

‹‹ብዙውን ጊዜ አርሶአደሮች መሬታቸው በአሲዳማነት ሲጠቃባቸው ማዳበሪያ አጥቶ ነው፤ መሬቴን በደንብ ስላላረስኩ ነው ብለው ያስባሉ። ማዳበሪያም ጨምረው፤ ምርጥ ዘርን ተጠቅመው ለምነቱን ለመመለስ ጥረት ቢያደርጉም ምርት ከመቀነስ ውጪ ሲጨምር አይታይም›› ሲሉ ከፍተኛ ተመራማሪው ይናገራሉ። በዚህ ችግር ምክንያት ከዚህ ቀደም ምርታማ የሚባሉ አካበቢዎች የተለያዩ ሰብሎችን ማምረት እስከ ማቆም የደረሱበት ሁኔታ መኖሩን ያስረዳሉ።

ለአብነትም የደጋማው የሃገሪቱ ክፍልን ነው የጠቀሱት። ‹‹እነዚህ አካባቢዎች ላይ አሲዳማነት በመብዛቱ ምክንያት ከዚህ ቀደም ይመረትባቸው የነበሩት እንደ ባቄላ፣ አተርና የመሳሰሉ ጥራጥሬ ሰብሎችን ማምረት እየቀመ ነው›› ይላሉ። በተለይ አተር አሲዳማነት በከፋባቸው ቦታዎች ላይ እየተመረተ አለመሆኑን ይናገራሉ። አሲዳማነት ከምርት መቀነስ ባሻገር ሰራም እንዳይበቀል፤ በአፈር ውስጥ የሚኖሩ ነፍሳት ሳይቀሩ እንዲሞቱ በማድረግ ከፍተኛ ጫና እንደሚያስከትል ዶክተር ገረመው ያስረዳሉ።

በሌላ በኩልም የማምረቻ ወጪ፣ ገንዘብና ድካም በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር እንደሚያደርግም ነው ያመለከቱት። ‹‹ከዚህ ቀደም ድሮ በተወሰነ የማዳበሪያ መጠን የሚገኘው ምርት አሁን ብዙ ማዳበሪያ መጨመርን ያስከትላል። ይህም የሚሆነው ንጥረ ነገር እጥረትን ስለሚያስከትል ነው›› ይላሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ከውጭ የሚገባው የማዳበሪያ መጠን በአብዛኛው ስራ ላይ እንደማይውል ጥናቶችን መሰረት አድርገው ይናገራሉ።

‹‹ባለፉት አራት ዓመታት በአሲዳማ አፈር የምንጠቀመው የማዳበሪያ መጠን በአብዛኛው ስራ ላይ እንደማይውል ጥናቶች ያሳያሉ›› በማለት ይጠቅሳሉ። በእነዚህ ዓመታት በአሲዳማ አፈር ምክንያት አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሚሆነው ማዳበሪያ ስራ ላይ አለመዋሉንም ነው ያስገነዘቡት።

ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የአፈር አሲዳማነት በተስፋፋባቸው የሃገሪቱ አካባቢዎች አሲዳማ አፈርን ለማልማት የተለያዩ ተግባሮች እየተከናወኑ ናቸው።

‹‹አሲዳማ አፈር ከታከመ ለስራ አመቺ ነው፤ ደግሞም በዝናብም ሆነ በደረቅ ጊዜ ሊታረስ የሚችል በመሆኑ ብዙ ጉልበት ሳይፈልግ በቀላሉ አልምቶ ማምረት ይቻላል›› ሲሉም ያመለክታሉ።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ አሲዳማነትን ከሚያባብሱ ነገሮች አንዱ ጥቅም ላይ የሚውሉ የማዳበሪያ አይነቶች ይጠቀሳሉ። በተለይ አሞኒካል ፈርትላይዘር የሚባሉ ማዳበሪያዎች አሲዳማነትን ስለሚያባብሱ የአፈርን ጤንነት ከመጠበቅ አኳያ የኬሚካል ማዳበሪያ አይደገፍም።

እሳቸው መፍትሄ ያሉትንም አስመልክቶው እንዳስታወቁትም፤ አርሶአደሩ ከኬሚካል ማዳበሪያ ወደ ተፈጥሮ ማዳበሪያ ማዞር አለበት። በአንድ ጊዜ ባይሆንም እንኳን በከፊል በመጠቀም ምርታማነትን ማሳደግ ጠቃሚ ነው። በተጨማሪም የሰብል ተረፈ ምርቶችን አሚጦ ከማሳ ላይ ባለመውሰድ የአፈር አሲዳማነት እንዳይበዛ መከላከል ይቻላል። በተጨማሪም ካልሺየም አክሳይድን የያዘ ማዳበሪያ ከኖራው ጎን ለጎን መጠቀም ዘላቂነት ያለው ምርት ማምጣትና የአፈሩንም ጤንነት ይዞ መቆየት ያስችላል። ከዚህ ባሻገርም በየቦታው የሚጣለውን የእንሳሳት አጥንት በመፍጨት ለማዳበሪያት መጠቀም ጠቃሚ ነው። ከዚሁ ጎን ለጎንም የአርሶአደሩን ግንዛቤ መጨመር ይገባል።

በዚህ ረገድም የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ላለፉት 12 ዓመታት የአፈር አሲዳማነት ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን በመገንዘብ ምርምሮችና ሙከራዎችን ማድረጉን ከፍተኛ ተመራማሪው ይጠቁማሉ። በዋነኝነትም የግብርና ኖራን ከአፈር ጋር ቀላቅሎ የአፈር አሲዳማነትን ማከም፤ ለሰብሎች ተስማሚ ሁኔታ እንዲፈጠር የማድረግ ስራዎች በሰፊው መሰራታቸውን ያስረዳሉ። ‹‹ይህንን በመስራታችን ለብዙ አርሶአደሮች ተደራሽ አድርገን የተጎዳ አፈር እንዲለማ፤ ምርታማነት እንዲጨምር በተለይ በገብስ በስንዴና በበቆሎ፤ በአኩሪ አተርና በባቄላ ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል፤እንደሃገር አሲዳማ አፈርን በኖራ የማከም ስራ ከተጀመረ ወዲህ የአርሶአደሩ የምርታማነት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል›› በማለትም ያብራራሉ።

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ የግብርና ኖራ በዋነኝነት የሚጠቅመው ማዳበሪያን ለመተካት ሳይሆን የአፈሩን አሲዳማነት ለማከም ነው። በአሲድ ምክንያት ሰብሎችን የሚያቀጭጨውንና በአሲዳማ አፈር ውስጥ የሚገኘውን የአልሙኒየምና የናይትሮጂንአዮን የተባለውን ንጥረ ነገር እንዲቀንስ ያደርጋል። ኖራ የአልሙኒየሙን ወደ ሌላ ንጥረ ነገር ቀይሮ የአፈርን ምርታማነት ከፍ የማድረግ ስራም ይሰራል። ይሄ በመሆኑ የሰብሎች ስር ጎዳት ይቀንሳል፤ በአፈር ውስጥ የጠፋውን ማግኒዢየምና ካልሺየም ይመልሳል። ከዚህም ባሻገር ሰብሉ የተጨመረለትን ማዳበሪያ በአግባቡ ተጠቅሞ የራሱን እድገት የማፋጠን ስራ እንዲሰራ ሚና ይጫወታል።

‹‹የኢንስቲትዩቱ ዋነኛ ተልዕኮ ቴክኖሎጂ ማፍለቅ ነው፤ በዚህ መሰረት ባለፉት 12 ዓመታት የኖራ ቴክኖሎጂን በማፍለቅ በኢንስቲትዩቱ ስር ባሉ 11 ማዕከላት ላይ ለሚገኙ 11ሺ 105 አርሶአደሮች በኩታ ገጠምም ሆነ በሰርቶ ማሳያ በቀጥታ እንዲተዋወቅ ተደርጓል›› ይላሉ። በተጨማሪም በተከናወነው የምርምር ስራ 4ሺ 463 ሄክታር የአርሶአደሩ ማሳ አገግሞ ምርት መስጠት እንዲችል መደረጉን ይጠቁማሉ። ይህም በክልሎች፣ በክልል የግብርና ምርምር ተቋማት፣ ግብርና ቢሮዎች፤ በዩኒቨርሲቲዎችና በሌሎች ተቋማት የተሰራውን አይጨምርም።

አሁን ላይ የግብርና ሚኒስቴር ይህንን መነሻ በማድረግ አሲዳማ አፈርን በኖራ የማከም ተግባርን ከፍተኛ ስራ አድርጎ በክልል ግብርና ምርምር፤ በዞንና በወረዳዎች ላይ እስከ 200 ሺ ሄክታር እንዲታከም እቅድ ይዟል። ለዚህም አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በጀት ተመድቦ እየተሰራ ነው።

ከዚህ በተጓዳኝ ቅንጅታዊ አሰራር ተግባራዊ መደረጉን ይጠቅሳሉ፤ ‹‹የኖራና የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) ተጠቅሞ የአፈርን ምርታማነት ለመጨመር በከፍተኛ ደረጃ እየሰራን ነው። ዘንድሮ በተወሰኑ ማሳዎች ላይ ሰፋ አድርገን በሰርቶ ማሳያ እየሰራን ነው›› ይላሉ። ይህም የተሻለ ምርት እንዲገኝ ከማድረጉም ባሻገር ወጪ ቆጣቢና አርሶአደሩ በቀላሉ ሊጠቀም በሚችለው መልኩ የሚከናወን መሆኑን ያስረዳሉ። በተጨማሪም አሲዳማነት የሚቋቋሙ ሰብሎች ላይ ትኩረት ያደረጉ የምርምር ስራዎች እየሰተሩ መሆናቸውን ያመለክታሉ።

‹‹አሲዳማነትን የሚቋቋሙ ሰብሎችን በመለየት ለአርሶአደሩ የማቅረብ ስራ ይሰራል። ከዚህ ቀደምም አራት አሲዳማነትን የሚቋቋሙ ሰብሎችን አውጥተናል፤ ከእነዚህም ውስጥ አንድ የስንዴ ዝርያና ጣፋጭ የሆነ የግብጦ ዘር አውጥተን አርሶአደሮች በስፋት እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ›› ሲሉ ይጠቅሳሉ። በተጨማሪም በ2016 ዓ.ም አንድ የተልባና አንድ የጎመን ዝርያ ማውጣቱን ይጠቁማሉ። በ2017 በጀት ዓመት ደግሞ የዘር ማባዛቱን ስራ በመስራት ለገበሬዎች የማስተዋወቅ ስራ እንደሚጀምር ነው ያመለከቱት።

ከዚህ በተያያዘም አንድ የድንች ዝርያም በምርምር ሂደት ላይ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ገረመው፤ በቅርቡ ይወጣል ተብሎ እንደሚጠበቅና ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ እንደሚሰራ ተናግረዋል። ኢንስቲትዩቱ በድምሩ ወደ ሰባት ዝርያዎችን ማውጣቱን ጠቅሰው፤ በቀጣይም ምርታማነትን የሚያሳድጉና አርሶአደሩን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የምርምር ስራዎችን በማከናወን የበኩሉን ኃላፊነት እንደሚወጣ አስታውቀዋል። እንደሃገርም ዘላቂ የሆነ ምርታማነት እንዲመጣ ከተፈለገ የአፈርን ጤንነት ማስጠበቁ ላይ ትኩረት ተደርጎ ሊሰራ እንደሚገባ ነው ያስገነዘቡት።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## ‹‹ትውልዱን ከቴክኖሎጂ ጋር ማላመድ ጊዜ የማይሰጥ ሥራ ነው››

**ቦጋለ አበበ**

ታላቁ ሊቅ ዶክተር እጓለ ገብረዮሐንስ የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ በሚል ርእስ በ1956 ዓ.ም ካሳተሙትና አሁን ላይ እንደ ክላሲክ ድርሳን በሚታየው መጽሐፋቸው «ትምህርት ከሰው ሥራ ወይም ከሰው ሕይወት ከዋነኞቹ ክፍሎች አንዱ ነው። ስለዚህ በተለይ ሊጠና ሊመረመር ይገባዋል» ሲሉ ይገልጹታል። ትምህርት የሰው ልጅ በዘመናት መካከል በብዙ ጥረትና ድካም ያገኛቸው ያከማቻቸው የዕውቀት ዘርፎች ተቀምረው፤ ተተንትነውና ተደራጅተው የሚገኙበት መስክ፣ ይህም የተገኘና የተደራጀ ዕውቀት በተሟላ መልኩ ለትውልድ ማስተላለፊያ ነው።

ታላቁ አሪስቶትል “ሜታፊዚክስ” በተባለው ድርሳኑ መግቢያ ላይ፣ “የሰው ልጅ በተፈጥሮው ለማወቅ በብርቱ የሚሻ ፍጥረት ነው" ይላል። ትምህርት ደግሞ የሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎት ሕሊናውን እና ልቦናውን ከነካው ጊዜ ጀምሮ ዘወትር በንቃት እና ያለ ዕረፍት ባለመታከት ያስገኘው እንዲሁም ያደራጀው ዋናው የሕሊናው ፍሬው ነው።

በመሠረቱ፣ ስለ ትምህርት ትክክለኛ አስተያየት ከተያዘ እና በቂ ትኩረት ከተቸረው ደግሞ ማንኛውንም የሕይወት ችግር ሊፈታ መቻሉን ለአቅመ ማሰብ የደረሰ ሁሉ የሚጠፋው ሃቅ አይሆንም። ትምህርትም ከሰው ልጅ የሕይወት ጥረቶች ውስጥ እንደ አንዱ እንደመሆኑ ከዘመንና ከቦታ ጋር የተቆራኘ ነው።

ትምህርት ምንጊዜም ቢሆን ከዘመንና ከቦታ ጋር የተያያዘ ነውና እንደቦታውና እንደዘመኑ የሚገጥሙትም ችግሮች የተለያዩ ይሆናሉ። በዚህ ሂደት አዳዲስ ችግሮች በየጊዜው እንደማጋጠማቸው ጊዜያቸውን የዋጁ አዳዲስ መፍትሄዎች ማስፈለጋቸው ከጊዜ ወደጊዜ ይበልጥ ግልጽ እየሆነ መጥቷል።

በዚህ ረገድ የጊዜያችን እና የወደፊቱ ጊዜ የትምህርቱ ዘርፍ ዋነኛ ተግዳሮት ሆኖ የሚዘልቀው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚያስከትለው ተጽእኖ መሆኑ በገሀድ እየታየ ነው። ሰው ሰራሽ አስተውሎት ደግሞ የቴክኖሎጂውን ተፅእኖ በግልፅ በማስመልከት ላይ ከሚገኙት ፈጠራዎች ዋነኛው ነው።

ለመሆኑ ሰው ሰራሽ አስተውሎት እንደ ሌሎች ሁሉ ለትምህርት ዘርፉ የሰጠው ፈተናና እድል ምን ይሆን? ሀገር በተለይም ቴክኖሎጂውን ጥቅም ላይ ለማዋልና መልካም በረከቱን እንድትቋደስ ምን ማድረግ ይገባል? ከሰሞኑ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች ይፋ የሆነው “ቨርቹዋል አጋዥ ወይንም አስጠኚ” ቴክኖሎጂው ለትምህርት ዘርፉ ምን ይዞ መጥቷል የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ከዩኒቨርሲቲው መምህርና ከቴክኖሎጂው ፈጣሪ ሕዝቅያስ ታደሰ ጋር ያደረግነውን ቃለምልልስ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

### ሰው ሰራሽ አስተውሎና ትምህርት

ባለንበት ፈጣንና ተለዋዋጭ የዲጂታል ዘመን ሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI) ከጤናው መስከ እስከ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ፣ ከንግድ እስከ የመጓጓዣ ተሽከርካሪ ኢንዱስትሪው መላውን የዓለም ሕብረተሰብ ገጽታ በመቀየር ላይ ይገኛል። በዚህ ረገድ ወደ አዕምራችን ቀድመው ከሚታወሱ ጥያቄዎች ውስጥ የትምህርቱ ነገርስ? የሚል ነው።

ቴክኖሎጂ እያንዳንዱን የሕይወት ዘርፍ መልሶ በማበጀትና በመበየኑ ረገድ ወሳኝ በሆነበት በዚህ ዘመን የትምህርትም እጣ ፈንታ ከዚ የራቀ ሆኖ አይገኝም። ዘርፉን እንዴት ነው የሚነካው የሚለውን ጉዳይ አሁን ላይ በቅጡ ለመበየን ቢከብድም፣ የትምህርቱን ሥርዓት በበጎም ይሁን በመጥፎ የመለወጥ አቅሙን መካድ ግን አይቻልም።

በትምህርቱ ዘርፍ ያለው ተፅእኖ ለመረዳት በተለይም በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የተደረገ አንድ ጥናት መመልከት በቂ ነው። ተማሪዎች ላይ በተካሄደው በዚህ ጥናት ከ 90 በመቶ በላይ የሚሆኑት ሰው ሰራሽ አስተውሎት እንደ አጋዥ የማስተማሪያ ቁስ መካተቱ ለመማርና ለማወቅ ባላቸው ተነሳሽነትና የትምህርት ተሳትፏቸው ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ተፅእኖ እንደፈጠረላቸው መናገራቸውን አመላክቷል።

ከዓለም አቀፉ የቴክኖሎጂ ማህበር (ISTE) የተገኘ ሌላ ጥናት ደግሞ ሰው ሰራሽ አስተውሎትን በትምህርት ውስጥ መገልገል የተማሪዎችን አፈጻጸም/performance እስከ 30 በመቶ እንደሚያሻሽለው ይፋ አድርጓል። ከተማሪዎች ባሻገር መምህሩ ላይ ያለውን ተፅእኖ በሚመለከት ሚኬንዚ/McK-insey ባካሄደው ጥናት ደግሞ፣ የተወሰኑ ስራዎችን ብቻ በሰው ሰራሽ አስተውሎት አውቶሜት/automate በማድረግ ብቻ በሳምንት እስከ 13 ሰዓት የሚደርስ የመምህራንን የስራ ጫና መቀነስ እንደሚቻል ተጠቁሟል። ይሄም የመምህራንን የሥራ ጫና በመቀነስ መምህራኑ ይበልጥ ወሳኝ በሆኑ ሥራዎች ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግ ያስችላል ይላል ።



**የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ መምህር ሕዝቅያስ ታደሰ፤**

በተመሳሳይ በኢስኩል ኒውስ/eSchool News የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው ከሆነም፣ 47 በመቶ የሚሆኑት የትምህርት ተቋማት መማር ማስተማሩን ለማጎልበት ሰው ሰራሽ አስተውሎትን እንደመፍትሔ መጠቀማቸውን ይገልፅልናል።

### የቴክኖሎጂው የገንዘብ አቅም

በዘርፉ የሚንቀሳቀሰውም ገንዘብ ለሰው ሰራሽ አስተውሎት እየተሰጠ ያለውን ልዩ ትኩረት በይበልጥ የሚያሳይ ነው። ለዚህም ማሳያ መጥቀስ ይቻላል። ለአብነትም ሆለንአይኪው/HolonIQ ባወጣው ሪፖርት መሠረት በ2025 ዓ.ም. በዓለም አቀፍ ደረጃ በትምህርቱ መስክ ብቻ ለሰው ሰራሽ አስተውሎት ኢንቨስት የተደረገው አጠቃላይ ወጪ 6 ቢሊዮን ዶላር እንደሚደርስ ያስቀምጣል።

### ሰው ሰራሽ አስተውሎት ስጋት ወይስ በረከት

ሰው ሰራሽ አስተውሎት በሁለት የአመለካከት አዝማሚያዎች መካከል ተወጥሮ ይገኛል። ማለትም ለትምህርት ዘርፉ ስጋት ወይስ በረከት? የሚለውን በመበየኑ ረገድ በዋናነት ሁለት ተፎካካሪ ሙግቶች ይቀርባሉ።

በአንድ ወገን ቁሱን በዓለም ዙሪያ ላሉ በርካታ የትምህርቱ ዘርፍ ማነቆዎች እና ፈተናዎች ሁሉ መፍትሄ ይሆናል ብለው የሚያምኑና የሚሞግቱ በርካቶች ናቸው። በአንጻሩ ይህን እሳቤ የሚቃረኑ ሌላ ጽንፎችና በተለይም በትምህርት ቤቶች Chat GPT (በህዳር ወር 2022 እ.ኤ.አ. ኦፕንኤአይ በተሰኘ ድርጅት የተለቀቀ የሰው ሰራሽ አስተውሎት መጠሪያ ስያሜ ነው) እንዲታገድ ጥረት ያደረጉ ተጠራጣሪዎችም ይስተዋላሉ።

እዚህ ጋር በተለይም ሊቁ ዶክተር እጓለ ገብረ ዮሐንስ “አንድ ሰው ለራሱ የማይመስለውን ነገር ለማፍረስ ብቻ ይሰለፋል። ሌላው ደግሞ ማፍረስን ለሌላው ትቶ በገዛ ሃሳቡ መሠረት አዲስ ለመገንባት ብቻ ያስባል። የተሻለው ዘዴ ሁለተኛው ይመስለናል።” ያሉትን ተከትሎ እያሰላሰሉ መራመድ አግባብ ሆኖ ይገኛል።

ይህ ማለት የኛም ጥረት በገዛ ሃሳባችን መሠረት አዲስ ቤት ለመሥራት እንጂ በአሮጌ ቤት የሚኖረውን ሰው ተጠግተን 'ቤትህ የማይረባ ነው' ለማለት አይደለም። ከዛ ይልቅ ሊቁ እንዳሉት “ከበረቱት አጠገብ አዲስ ቤት መሥራት ነው። ይህ አዲሱ ቤት ስለራሱም አዲስነት ስለሌላውም አሮጌነት ብቻውን ይናገራል።” ብለን በክርክሩ በቀጥታ ከመሳተፍ ይልቅ ሰው ሰራሽ አስተውሎት እንዴት ለዘርፉ በረከት እንደሚሆን ወይም መሆን እንደሚችል ለማመላከት በመስክ የተፈተነውን የጥረታችንን የመጀመሪያ ሙከራ መመልከት እንችላለን።

### የዲጂታል አጋዥ ወይንም አስጠኚ ውልደት

በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች ይፋ የሆነው “ቨርቹዋል አጋዥ ወይንም አስጠኚ” የቴክኖሎጂው ፈጣሪዎች ጥረት መነሻ በፈተና ዝግጅት ወቅት ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸው ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች እንዴት መሻገር ይችላሉ ማለትን ታሳቢ ያደረገ ነው። እንደሚታወቀው በሀገራችን ያነበቡትን በቅጡ መረዳት ብሎም በማስታወስና ጊዜን በአግባቡ ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት የመመደብ ድክመት እንዲሁም የሚነበቡ መጻሕፍት መብዛት ወደ አካዳሚክ ስኬት የሚደረገውን ጉዞ ፈታኝ እንደሚያደርጉት ይታወቃል። ተማሪዎች ለከፍተኛ ተቋም መውጫ ፈተና የሚዘጋጁ ከሆኑ ደግሞ የሚያጋጥሟቸው ችግሮችና ፈተናዎች ይበልጡኑ ያይላሉ።

በዚህ ረገድ ያነበቡትን በቅጡ ለመረዳት መቸገርን ጨምሮ ያነበቡትን ለማስታወስ መቸገር፣ ጊዜን በአግባቡ ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት መመደብ አለመቻል፣ የበዙ የሚነበቡ መጻሕፍትን፣ ሞጁሎችን፣ ሃንድ አውቶችንና የማጣቀሻ መጻሕፍትን አንብቦ ለመሸፈን መቸገር ድረስ ለከፍተኛ ተቋም መውጫ ፈተና የሚሰናዱ ተማሪዎችን ሲገጥም የሚስተዋል ስር የሰደደ አይነተኛ ችግር ነው።

እነዚህንና መሰል የተማሪዎችን ችግሮች ለማቅለል በፈተናዎቻቸውም የላቀ ውጤት እንዲያመጡ ለማገዝና ለማስቻል አዲስ ችግር ፈቺ መፍትሄ ማስፈለጉ የሚያከራክር አይደለም። በዚህ ረገድ ዘርፈ ብዙ ጥናትን ምርምር በማድረግ መፍትሄ ይሆን ዘንድ “ቨርቹዋል አጋዥ ወይንም አስጠኚ” ቴክኖሎጂውን ማበልፀግ አስፈላጊ ሆኗል። ይህ መፍትሄ ‹‹ቨርቹዋል አጋዥ ወይንም አስጠኚ/AI-powered chatbot/Personal Learning Companion Chatbot ይሠኛል።

ይህ ጅምር የቴክኖሎጂ ቁስ ለትምህርታዊ ዓላማ እንዲውል የሰው ሰራሽ አስተውሎትን (AI)ን አቅም በመጠቀም ለመውጫ ፈተና ለሚዘጋጁ ተማሪዎች እንደ ረዳት መምህር ወይም አስጠኚ ሆኖ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ነው። በአጭሩ የተማሪው ቨርቹዋል አጋዥ/ደጋፊ ወይንም አስጠኚ ልንለው እንችላለን። በቅርቡ በተለያዩ አካባቢዎች ለተማሪዎችም ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል።

በዚህም ከላይ ለተጠቀሱት መሰል ችግሮች መፍትሔ ለመፈለግ የሚደረገውን ጥረት ለመርዳት በቴክኖሎጂው አበልጻጊዎች ብዙ ጥረት ተደርጓል። ቴክኖሎጂው ለመጀመሪያ ጊዜ የተሞከረ እንደመሆኑ ከስህተት ፈፅሞ የራቀ ነው ለማለት ግን አያስደፍርም። የቴክኖሎጂው አበልጻጊዎች ዶክተር እጓለ እንደሚሉት፣ ‹‹ምንም ባናስገኝም ጥረታችን ይበቃናል››። የሚል እምነት አላቸው።

ይሁንና የውጤታማነትና የተግባራዊነት ስኬታቸው በተማሪዎቻቸው ሚዛን የሚለካ ነው ባይ ናቸው። የቴክኖሊጂው የእገዛ አቅምም ከራሳቸው ተማሪዎች አንደበት ማረጋገጥ የሚቻል ነው ይላሉ። (ይህን ቨርቹዋል አጋዥ ወይንም አስጠኚ መመልከት አልያም መሞከር የሚፈልግም በዚ መስፈንጠሪያ link: https://www.temaribet.edu.et/) በመግባት መመልከትና መሞከር እንደሚችል ይጠቁማሉ።

በጥቅሉ የቴክኖሎጂው ዓላማ ለመውጫ ፈተና የሚዘጋጁ ተማሪዎችን ማገዝ እናም ለብሔራዊ የመውጫ የፈተና ሥርዓት-ትምህርት የተዘጋጁ አጠቃላይ የጥናት መሣሪያዎችንና መርጃዎችን ማቅረብ ሲሆን የሚከተሉትንም ዝርዝር ፋይዳዎች ይሰጣል።

### የቴክኖሎጂው ፋይዳዎች

በዋናነት ጥያቄዎችን ይመልሳል። ማብራሪያዎችን ይሰጣል። የመለማመጃ ጥያቄዎችን ያዘጋጃል። የተለያዩ የጥናት መረጃዎችን ጨምሮ ወርክሾፖችን፣ ግራፊክ ኦርጋናይዘሮችን፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ኔሞኒክ ዲቫይሶችን ያዘጋጃል። ከዚህ ባሻገር የአጠናን ስልትን ይቀይሳል። የጊዜ አጠቃቀም መመሪያዎችንና የጥናት ልምድን ለማሻሻል የሚበጁ መመሪያዎችን ይነድፋል።

ይህ ቨርቹዋል አጋዥ ወይንም አስጠኚ ቴክኖሎጂ ከብሔራዊ ፈተና ሥርዓተ ትምህርት ጋር ተስማምቶ በመዘጋጀቱም ተማሪዎች ውስብስብ የሆኑ ጽንሰ-ሀሳቦችን በትክክልና በቀላሉ እንዲገነዘቡ የሚረዱ ዝርዝር ማብራሪያዎች፣ ምሳሌዎችና የማስታወሻ ዘዴዎችን በመስጠት ተማሪዎችን ለመውጫ ፈተና እንዲዘጋጁ ያደርጋል። በመሰል አበርክቶውም ተማሪዎች ለመውጫ ፈተና በሚገባ እንዲዘጋጁና በራስ የመተማመን መንፈሳቸውም ከፍ እንዲል እንዲሁም ውጤታማ እንዲሆኑ ይረዳል።

ይህ ቨርቹዋል አጋዥ ወይንም አስጠኚ በበይነ መረብ/ኢንተርኔት ግንኙነት ማንኛውንም ተማሪ ለመውጫ ፈተና እንዲዘጋጅ ያደርጋል። ከባህላዊ የጥናት ዘዴ በተለየ መልኩ ተማሪውን 24/7 እንዲያግዝ የተዘጋጀ ቨርቹዋል አጋዥ ወይንም አስጠኚ የእያንዳንዱን ተማሪ የተለያየ የመረዳት ዝንባሌ እና ስልት ብሎም የመማርና የመገንዘብ ፍጥነት ባገናዘበ መልኩ በልፅጎ መዘጋጀቱም ልዩ ያደርገዋል።

### ቴክኖሎጂዎቱ ላይ የሚስተዋሉ ድክመቶች

የዚህ አይነት የሰው ሠራሽ የማሰብ ችሎታን የሚጠቀሙ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ላይ የሚቀርቡ ትችቶችንና ነቀፌታዎች አሉ። በአብዛኛው የሰው ሠራሽ የማሰብ ችሎታን የሚጠቀሙ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚያመነጩትን አልያም የሚሰጡትን ምላሽ (response) በተመለከተ በስፋት የሚነሳው ነቀፌታ የይዘቱን ጥራት የተመለከተ ነው። በዚህ ረገድ ተደጋግመው ከሚሰሙ የተቃውሞ ድምጾች ውስጥ ‘በኤ አይ የሚመነጭ ነገር ጥራት ይጎድለዋል፣ ውጤቶቹ ተዓማኒነት ይጎድላቸዋል’የሚሉት ጎልተው የሚሠሙ ናቸው።

ይሁን እንጂ ይህ ዓይነት ችግር ይፋ በተደረገው ቴክኖሎጂ ላይ እንደማይስተዋል አበልፃጊዎቹ ሙሉ እምነት አላቸው። ምክንያታቸውም ይህንን አሳሳቢ ችግር አስመልክቶ ቀደም ብለው መፍትሔ ማበጀት መቻላቸው ነው። ይህ ቨርቹዋል አጋዥ ቴክኖሎጂ የሚያጣቅሰው እያንዳንዱ የዕውቀት ቋቱ (knowledge base) የተደራጀው በጥንቃቄ ለመውጫ ፈተና ዝግጅት ተብሎ በከፍተኛ ተቋም መምህራን በተዘጋጀ፣ ከእነሱም በተሰበሰበ፣ የእነሱንም ይሁንታ ባገኘ የሰነዶች ስብስብ ግብአትነት በመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች ጋር እንዳይተዋወቅ ያደርገዋል። በዚህም ለተፈታኝ ተማሪዎች ለፈተናቸው በቀጥታ የሚጠቅሙ፣ ትክክለኛና ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ምላሾች ያቀርባል።

በመሠረቱ፣ በአሁኑ ወቅት የበዙ ተማሪዎች በልማዳዊው የአጠናንና የፈተና ዝግጅት ዘዴዎች በትምህርታቸው ስኬታማ ለመሆን ሲቸገሩ ይስተዋላል። ቨርቹዋል አጋዥ እውን መሆን ለዚህ ትልቅ መፍትሄ ነው። በተለይም የተማሪዎችን ተሳታፊነት በማሳደጉ፣ የመረዳት ደረጃቸው መለያየቱን አልያም በተለያየ የመረዳት ደረጃ ላይ መገኘታቸውን ታሳቢ በማድረጉ፣ የእያንዳንዱን ተማሪ የተለያየ የመረዳት ዝንባሌ እና ስልት በመለየቱ፣ ለሁሉም ተደራሽ በመሆኑም ተመራጭ እና ጊዜውን የዋጀ ያደርገዋል።

### ቀጣይ እርምጃና ፍላጎት

ይህ ጥረት ጅማሬ እንጂ ፍጻሜ አይደለም። በአሁኑ ወቅት የአንደኛ ደረጃ ማጠቃለያ ፈተና ለሚወስዱና ወደ ከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተና ለሚወስዱ ተማሪዎች ማለትም ለ8 ተኛ እና ለ12ተኛ ክፍል ተፈታኝ ተማሪዎች አዲስ ቨርቹዋል አጋዥ ወይንም አስጠኚ እያዘጋጁ ይገኛሉ። መሰል የቴክኖሎጂ በረከት ለሁሉም የሀገሪቱ ተማሪዎች ለማድረስ የሚደረግ ጥረት ግን መንገዱ አልጋ በአልጋ አይደለም። እዚህም እዚያም ማነቆዎች ያጋጥማሉ። የቴክኖሎጂው አበልጻጊዎችም የዚሁ ፈተና ተጋፋጮች ናቸው።

ትምህርቱን ብሎም ትውልዱን የማገዝና የመደገፍ መሰል ቅን ሃሳብ በተናጠል ጉዞና ከባለድርሻ አካላት ትኩረትና ድጋፍ ውጪ ብዙ ርቀት መራመድ አይቻለውም። ይህ እንደመሆኑም ከሁለንተናዊ ፋይዳው አንፃር ቨርቹዋል አጋዥ ወይንም አስጠኚም ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን የበርካቶች የሃሳብም ሆነ የገንዘብ ድጋፍ ይሻል።

### ትምህርት እና መጪው ጊዜ

በመሠረቱ፣ ትምህርት ከዘመን ዘመን እየተሻገረ አሁን ላይ የደረሰውን ዕውቀት መጠበቂያና እና መንከባከቢያ እንዲሁም በተሟላ መልኩ ለትውልድ ማሳወቂያና ማስተላለፊያ እንደመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚሻ መሆኑ ማንም የሚያውቀው ሃቅ ነው።

የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ እድገት እውን ማድረግ የሚቻለውም ከሁሉ በላይ በትምህርት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። የትምህርት አንዱ ዓይነተኛ ዓላማ ደግሞ ጊዜው የሚጠይቀውን እውቀትና ችሎታ በማስታጠቅ ትውልዱን ዘመን ይዞ ለሚመጣበት ፈተናዎች ማዘጋጀት፣ በጥቅሉ ለወደፊት ኑሮው ማሰልጠንና ብቁ ማድረግ ነው። ይህም የመጪውን ጊዜ ፈተና አሁን ላይ ሆኖ መተለምን፤ ይህንንም ትልም የትምህርቱ ስልቶች አድርጎ መንደፍን፤ ትውልዱንም ለዚህ ማዘጋጀትን ሁሉ የሚያካትት ተግባርን ይሻል።

መጪው ጊዜ ደግሞ ሰው ሰራሽ አስተውሎት በብዙ የሕይወት ዘርፎች የሚነግስበት ዘመኑም ዘመነ ኤአይ እንደሚሆን ለመገመት ብዙ ፍንጮች ስላሉ ነብይ መሆንን አይጠይቅም። ስለዚህ ትውልዱን ለእነዚህና መሰል ዘመኑ ይዞት ከሚመጣው የዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር ማላመድ እጅግ አስፈላጊ እና ጊዜ የማይሰጥ ስራ ነው። ከሁሉ በላይ የቴክኖሎጂን መልካም ስጦታ ለመቀበል መዘጋጀት ያስፈልጋል።

ሊቁ ዶክተር እጓለ ገብረዮሐንስ “አንድ ሰው ወይም ሕዝብ በመሻሻል ወደፊት ለመራመድ ያለውን ምኞትና ናፍቆት በሥራ ለማዋል መፈለጉ የሚታወቀው ለወጣቱ ትውልድ የትምህርት ዓላማ ይሆን ዘንድ በሚወስነው ነገር ነው”። ማለታቸውን ለትምህርት መድከም/መጣር ምንኛ የተገባ እንደሆነ ጠንቅቆ ይገባን ዘንድ ማስታወስ ተገቢ ይሆናል።

# ወቅታዊ

# ‹‹ኢትዮጵያ ከተማ መር የልማት አቅጣጫ በመያዝ እየለማች ነው››


- ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ሊሬቦ
በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይንና ፕላን መምህር

በኃይሉ አበራ

ካለ ከተሞች እድገት ያደገ ሀገር እንደሌለ መረጃዎች ያመላክታሉ። ከተሞች ለሀገር እድገት ሰፌ ሚና ያላቸው በመሆኑ የከተሞች መሰረተ ልማት ዕድገት ወሳኝ ነው። በኢትዮጵያ በየዓመቱ በብዙ ሚሊዮን ወደ ከተሜነት እየተቀየረ ነው። የሀገራችን ፈጣን የከተሜነት መስፋፋት በተገቢ መሰረተ ልማት ሲመራ የሚገባ መሆኑን የከተማ ልማት ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

በፍጥነት እያደገ ያለውን ከተሜነት በአግባቡ ማስተዳደር ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ነው። ከተሞች የአንድን ሀገር እድገት ወይም ልማት ሲወስኑ የሚችሉ የልማት ሞተሮች ናቸው። ስለዚህም ዜጎች ከከተሞች ትሩፋት መጠቀም እንዲችሉ ከተሞች በፕላን ሲመሩ ይገባል። የከተማ ነዋሪው የተሟላ ኑሮ እንዲመራ፣ ምርታማ ዜጋ እንዲሆን ደረጃውን የጠበቀ መኖሪያ ቤት ውስጥ መኖር ይኖርበታል። አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች የተሟሉለት መሆን አለበ። እይቀሬ ከሆነው ከተሜነት አኳያ በተለይ አዳዲስ የከተማ ማዕከላትም ከምስረታቸው ጀምሮ በእቅድ ሲመሩ ዝግጁ መሆን አለባቸው።

በአጠቃላይ በከተማና ከተሜነት እንዲሁም የዚሁ አንድ አካል የሆነው በአዲስ አበባ እና በክልል ከተሞች እየተተገበረ ስለሚገነው በኮሪደር ልማት ዙርያ በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ሊሬቦ (ዶ/ር)፣ ጋር ቆይታ አድርገናል። መልካም ንባብ።




**አዲስ ዘመን ፡-የኢትዮጵያን የከተሞች አመሰራረት ምን ይመስላል? ከተሞች የልማት ማዕከልነታቸውስ እንዴት ይገለጻል?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል፡-** የሀገራችን የከተሞች አመሰራረት የሌሎች ሀገራት ከተሞች ከተመሰረቱት የተለየ ነው። በሌላው ዓለም ላይ ያሉ ከተሞች በማኑፋክቸሪንግ፣ በኢንዱስትሪ የተመሰረቱ ናቸው። የሀገራችን ከተሞች ካለ ኢንዱስትሪ፣ አለ ማኑፋክቸሪንግ የተመሰረቱ ናቸው ተብሎ ይወሰዳል። እንደ ቁልቢ ገብርኤል ያሉ ከተሞች በሃይማኖት ምክንያት የተመሰረቱ ሲሆን፤ የሀዋሳ ከተማ የመሳሰሉት ደግሞ በአስተዳደራዊ ማዕከልነት የተመሰረቱ ናቸው። ሌላው ደግሞ ንግድ ወይ ደግሞ የትራንስፖርት መንገድ ተከትሎ የተመሰረቱ ናቸው። ቢሾፍቱ፣ አዳማ ከተሞች የባቡር መንገድን ተከትለው ተመስርተዋል። በመሆኑም አሁን የአሀገራችን መንግሥት እያደረገ ባለው ጥረት የኢንዱስትሪ ፓርኮች እየተመሰረቱ ናቸው። ለስራ እድል ፈጠራ ፋብሪካዎችን የማቋቋም፣ ትላልቅ የስራ እድል ፈጣራ ስራዎች እየተፈጠሩ ናቸው።

ማኑፋክቸሪንግ እና ኢንዱስትሪ ሌሎች የዓለም ከተሞች የደረሱበትን ደረጃ ለመድረስ አንዱ ምክንያት ነው። አሁን ላይ ከዚህ ተሞክሮ በመውሰድ ሌሎች የዓለም ከተሞች እንዴት እዚህ ደረሱ የሚለውን በማየት ሀገራችንም ወደ እድገት ጎዳና በመግባት ላይ ነች። የኢንዱስትሪ ፓርኮች እየተቋቋሙ ነው። በከተሞች የቱሪዝም፣ የማኑፋክቸሪንግ፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ እንቅስቃሴ ላይ እየተሰራ ይገኛል። በመሆኑም በፍጥነት እያደገ የመጣውን የከተሜነት ጉዳይ ትኩረት በመስጠት በሥርዓት እና በእቅድ መምራት ይገባል።

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ግብርና መር አሁን ደግሞ የማኑፋክቸሪንግ ወይም ከተማ መር የልማት አቅጣጫ በመያዝ እየለማች ነው። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ከተሞች የሀገሪቱን የልማት አቅጣጫ የሚያመላክቱ ናቸው። በመሆኑም በሀገር ልማትና ዕድገት ላይ የከተሞች ሚና ሰፊ ድርሻ አለው። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የኢትዮጵያ የከተሞች ምጣኔ 25 በመቶ አካባቢ ደርሷል ተብሎ ይገመታል። የከተሜነት መስፋፋት ፍጥነቱም አምስት ነጥብ አራት በመቶ ነው። ይህም ሀገሪቱን በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈጣን የከተሞች እድገት ካለባቸው ሀገሮች ተርታ ያሰልፋታል። ይህ ፈጣን የከተሜነት እድገት በአግባቡ ከተመራ የሥራ ፈጠራ እና የኢኮኖሚ ብልጽግና ማዕከላት ይሆናሉ።

ከተሞች በፕላን ከተመሩ፣ የመኖሪያ፣ የመነገጃ፣ የማኑፋክቸሪንግና የሥራ ፈጠራ ማዕከላት የመሆን አቅም አላቸው። የኢትዮጵያን ብልፅግና እና ልማት ወደ ፊት ሊወስኑ የሚችሉ ስለሆኑ በአግባቡ ሊመሩ ይገባል። አሁን እየተካሄዱ ያሉት የኮሪደር ልማት እንቅስቃሴዎች ከተሞቹን በአግባቡ የመምራት መገለጫዎች ናቸው።

እንዲሁም ከተሞች የፈጠራ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም የተለያዩ ፈጠራዎች ማዕከላት ተብለው ይወሰዳሉ። ንፁህ አካባቢ መሆን አለባቸው፤ እግረኛ በነፃነት የሚንቀሳቀስባቸው፣ ወንጀለኛ የሌለባቸው፣ ደኅንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆኑ ይጠበቃል። ደረጃቸውን ጠብቀው ማደግም አለባቸው። ደረጃውን የጠበቀ መንገድ፣ የመብራት ዝርጋታ፣ የልጆች መጫወቻ ስፍራ፣ የአረንጓዴ ስፍራ፣ የቱሪስት መስህቦች፣ የመናፈሻ ስፍራዎች ለከተሞች ያስፈልጋሉ። ከዚህ አኳያ የሚሠሩ ሥራዎች ለመጪው ትውልድ ጭምር የሚሆን ከተማን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ደረጃቸውና ሥነውበታቸው ተጠብቆ መገንባት ይኖርባቸዋል።

የመሬት አጠቃቀምም በአግባቡ እና በሥርዓት መመራት አለበት። መንገዱን፣ መናፈሻ ስፍራውን፣ የንግድ ቦታውን ቅይጥ ቦታዎችን በአጠቃላይ የታሰበውን የትምህርት፣ የመዝናኛ፣ የሃይማኖት ስፍራዎችን በሙሉ ማኅበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ሕጋዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እንዲሁም ባህላዊ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት በፕላን መምራት ያሻል። ከዚህ አኳያ ሲታይ በአዲስ አበባ እየተካሄደ ያለው የኮሪደር ልማትም ከዚህ አኳያ እንደ ሞዴል የሚታይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከተሞች ከተማ ለመባል በመሰረታዊነት ምን ያስፈልጋቸዋል? የኢትዮጵያ ከተሞች ከዚህ አንጻር እንዴት ይታያሉ?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል፡-** አንድ ከተማ ከተማ ለመባል ጥራት ያለው መሰረተ ልማት የተዘረጋለት መሆን አለበት። ሰዎች ደግሞ ከግብርና ውጪ በሆኑ በማኑፋክቸሪንግ ውስጥ የሚሰሩ በአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ የሚሰሩ መሆን አለባቸው። ስለሆነም ከተማ የሚባለው አንዱ የንፁህ ውሃ መኖር፣ የመንገድ ድርና ማጉ የተሳለጠ መሆን፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል በቂ መሰረተ ልማት በአግባቡ የተሟላ እና የተደራጀ ከሆነ ነው። ይህ በመሆኑም ነው በገጠር የሚኖረው ሕዝብ ኑሮውን ወደ ከተማ እያደረገው የሚገኘው። በጥግጊት ደረጃ በአንድ ሄክታር ቢያንስ በትንሹ 100 ሰው የሚኖር ከሆነ ከተማ ይባላል። ሁለት ሺህ ሰው ሲባልም 20 ሄክታር ላይ ላይ ይኖራል እንደማለት ነው። በመቀጠልም ጥራት ያለው መሰረተ ልማት መኖር ነው። ሶስተኛው ደግሞ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው። ከተሞች የኢኮኖሚ፣ የገቢ ወጪ፣ የኢንዱስትሪ፣ የትምህርት፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማዕከላት ናቸው። በመሆኑም ከተማ ሲባል ይሄ ሁሉ አብሮ ተደራጅቶ ያለበት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሀገራችን ከተሞች ከአረንጓዴ ሽፋን፣ ከተለያዩ የመንገድ መሰረተ ልማቶች አኳያ ምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ፡-** የትኛውም ሀገር የልማቱ ምንጭ እና መሰረቱ ከተሞች ናቸው። ስለዚህ ከተሞቻችን በፕላን ይመሩ ተብሎ ሲታሰብ በመሰረተ ልማት፣ ውሃ፣ መብራት፣ ቴሌ፣ መናፈሻ ስፍራዎች፣ የልጆች መጫወቻ ስፍራዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ትምህርት ቤቶች በሙሉ የተሟላ መሆን ይኖርበታል። ከተሞች ንፁህ አካባቢ መሆን አለባቸው። እግረኛ በነፃነት የሚንቀሳቀስበት፣ ወንጀለኛ የሌለበት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ ከማድረግ ከዚህ አኳያ መስራት ይጠበቃል። በመሆኑም ደረጃውን የጠበቀ መንገድ፣ የመብራት ዝርጋታ፣ የልጆች መጫወቻ ስፍራ፣ የአረንጓዴ ስፍራ፣ የቱሪስት መስህቦች፣ የመናፈሻ ስፍራዎች ያስፈልጋሉ።

ከዚህ አኳያ የሚሰሩ ስራዎች ለትውልድ የሚሆነውን ከተማ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ደረጃቸውንና ስነውበታቸውን ጠብቀው መከናወን አለባቸው። በመሆኑም በፍጥነት እያደገ የመጣውን የከተሜነት ጉዳይ ትኩረት በመስጠት በሥርዓት እና በእቅድ መምራት ይጠይቃል። የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ከክልል፣ ከዞን እና ከወረዳ መንግሥታት እና አስተዳደሮች ጋር በመሆን መስራት ይኖርበታል።

ፕላን ሲሰራም በሀገራችን ባለው በከተማ መሰረተ ልማት የተቀመጠው ስታንዳርድ 30/30/40 ነው። 30 በመቶ የአረንጓዴ ለምለም እና መናፈሻ ስፍራዎች፣ 30 በመቶ የመንገድ ድርና ማግ እና የመኪና ማቆሚያ፣ 40 በመቶ ደግሞ ህንጻ የሚያርፍበት በሚል ክፍፍል ተቀምጧል። አረንጓዴ ለምለም ማለትም አሁን ዓለም ላይ እየመጣ ያለውን የአየር ንብረት ለውጥ ጭምር የሚቋቋም ነው። ሰው የሚኖርበት፣ የሚነግድበት፣ የሚዝናናበት፣ የአየር ንብረቱ የተስተካከለ ከተሞችን መፍጠር ይሆናል። ከዚህ አንፃር የወንዝ ዳር ልማት፣ የመናፈሻ ስፍራዎች እና የአረንጓዴ ለምለም ስፍራዎች በመንደር ውስጥ፣ በመሬት ላይ ብቻ ሳይሆን በህንፃዎች ሽቅብ ጭምር ያሉ የከተማ እርሻዎች፣ የምግብ ዋስትናን የሚያግዙ ናቸው።

የከተማ እርሻንም በማስፋፋት አረንጓዴ እርሻ ፣ የከተማ እርሻ፣ የከተማ ጫካ፣ የመንደር ውስጥ የመናፈሻ ስፍራዎች የወንዝ ዳር ልማትንም ጭምር በማሳለጥ ከተሞቻችንን በአረንጓዴ ለምለም ውስጥ እንዲገኙ መስራት ይኖርብናል። አረንጓዴ ለምለም በከተማ ውስጥ ሳይሆን (City in The Park) በሚለው ፅንሰ ሃሳብ በከተሞች ህንፃዎች ላይ ሁሉ አረንጋዴ ሆነው የምግብ ዋስትናንም በማረጋገጥ ከተሞቻችን የምንኖርበት እና ድህነት የሌለበት ከተሞችን ከመፍጠር አንፃር መስራት አለብን። አሁን የአረንጓዴ አሻራ የምንለው እና በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘው በዩኒቨርሲቲዎች፣ በመንግሥት አስተዳደር ፅህፈት ቤቶች ወስጥ፣ በተቋማት፣ በመንደር ውስጥ የአረንጓዴ ለምለም ዛፍ ብቻ ሳይሆን የሚመግብ ከተማ መፍጠር ይገባል።

**አዲስ ዘመን ፡- ከተሞቻችን እንዴት ይገለጻሉ? አሁናዊ ገጽታቸው ምን ይመስላል?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል፡-** አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ከተሞቻችን ሲታዩ በትክክል ልናስብ የሚገባው ጊዜ አሁን ነው። ጉድለት አለ፤ ከተሞች በፕላን እየተመሩ አይደለም። ዘላቂ የሆነ የመሬት አጠቃቀም በፕላን በማዘጋጀት የታሰበውን የመሬት አጠቃቀም ለታሰበው ዓላማ በማድረግ የዜጎችን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ በአግባቡ ሊሰራ ይገባል። አሁን ባለው ሁኔታ የፕላን ጉድለት አለ። አሁን አዲስ አበባ ላይ ሲታይም የፕላኑ አካል እንዲሆን ማስተካከያ እየተሰራ ነው ያለው።

የኮሪደር ልማት ቀደም ሲል በነበረው ክፍተቶች ነበሩበት። አሁን ሕግና ደንብ አድርጎ በማምጣት የከተማው ካቢኔም የፕላኑ አካል እንዲሆን በማድረግ የአዲስ አበባ የአስረኛ ፕላን ትግበራ አንዱ አካል ሆኖ እንዲመጣ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ‹‹ኢትዮጵያ ከተማ መር የልማት...

ከገጽ 9 የዞረ

ተደርጓል። በሌሎች ከተሞቻችንም አሁን የሚታየው ገፅታ ደካማ በመሆኑ ከዚህ ትምህርት በመውሰድ እና በመንቃት በትክክል ሊታሰብበት የሚገባ ነው። ማህበረሰቡ እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከተሞችን ለማስዋብ፣ ከተሞች የስራ ማዕከላት እንዲሆኑ፣ የውበት፣ የቱሪዝም ማዕከላት እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ አሁን መንቃት ይገባል። አሁን በየከተሞቻችን የሚታየው ደካማ አካሄድም እንዳለ ይቀጥል ወይስ ከዛ በመውጣት ራዕይ እና ፕላን ተግባራዊ በማድረግ እናልማቸው የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት። ስለሆነም ስንጓዝበት ከነበረው አካሄድ በመውጣት ስማርት ከተሞችን መፍጠር ተገቢ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- ከተሞችን ስማርት ሲቲ የማድረግ ስራዎች ይታያሉ፤ ስማርት ሲቲ ማለት ምን ማለት ነው፤ ስከተሞች ያለውን ፋይዳ ቢያብራሩልኝ? የእኛ ከተሞች በተለይ አዲስ አበባና አንዳንድ ሰፋፊ ከተሞች ከዚህ አኳያ ምን ደረጃ ላይ ናቸው?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ፡-** ስማርት ሲባልም ቅይጥ ነው። ስማርት ከተማ ሲባል በትንሽ ቦታ ላይ ብዙ ሰዎች እንዲኖሩ የማድረግ፣ ሰው ረጅም ርቀት እንዳይጓዝ በማድረግ፣ በአንድ ህንፃ ውስጥ ቢሮና የንግድ ስራ፣ መኖሪያ ያለበት የሚለውን ጭምር ያካተተ ነው። ከተማው ከወንጀል ነጻ የሆነ፣ ወንጀለኛ የሚጠፋበት፣ ከተማው ገላጣ የሆነ ለሁሉም ሲታይ በሲስተም የተቀናጀ፣ ዲጂታል የሆነ፣ በቴክኖሎጂ የሚመሩ ከተሞችን ከመፍጠር አኳያ እየተሰራ ያለበት ሁኔታ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ከተሞች ስማርት ናቸው ሲባልም ሰው ቀለል ያለ ኑሮ የሚኖርባቸው፣ መሬት አስተዳደር በመሄድ የመልካም አስተዳደር ችግር የተቀረፈበትና በቀላሉ በሲስተም የሚስተናገድበት፣ ወረቀት አልባ መስተንግዶ ያለበት ነው። ሰው በቀላሉ በአጭር ጊዜ የሚስተናገድበትን ሥርዓት በማምጣት በካዳስተር ሥርዓት በመሬት አስተዳደር እየተሰራበት ነው። ይህ ሲሆን ካርታ ለማሳተም መመላለስ ይቀራል። በትራንስፖርት ሲስተሙ ሰው ገጭቶ አይጠፉም፤ በሲሲቲቪ ካሜራ ከተማው በራሱ መቆጣጠር ይችላል። ለመብራት እና ውሃ መጨነቅ ይቀራል። ከዚህ አኳያ በተቋማት መሰረተ ልማቶችም ስማርት እንዲሆኑ ወይም ስልጡን እና ብልህ የሆኑ ከተሞችን ከመፍጠር አንፃር ተግባራዊ በማድረግ ከተሞቻችን አሁን ካሉበት ደካማ ሁኔታ ነቅተው ወደ ፍፁም እድገት መቀላቀል እንደሚገባ ማሰብ የሚገባበት ወቅት ላይ ነን።

በሀገራችን ስልጡን ከተሞችን ከመፍጠር አኳያ ጅማሮዎች አሉ። በ2025 ኢትዮጵያ ዲጂታል ሀገር እንድትሆን በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተቀመጠው አቅጣጫ የሚታወስ ነው። በቴሌኮም፣ በአርተፊሻል ኢንተለጀንስ እና በመሳሰሉት የተቀመጠውን ስትራቴጂ በመከተል ከተሞቻችንን ዲጂታላዝ የማድረግ፣ በኢንዱስትሪ፣ ኢትዮጵያ ታምርት፣ በኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ትገንባ ንቅናቄዎች ሚናቸው የዚህ አካል ነው። በመሆኑም በ2025 አንዱ አንዱን የማይጎዳበት ግልፅ አሰራር ያለበትን ቅልጥፍና ለማምጣት ተግባራዊ የሚሆንበት እና ማዘጋጃ ቤቶቻችን የስማርት ከተማ አስተሳሰቡን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል።

በገቢ አሰባሰብ፣ በውሃ እና በመብራት፣ በባንኮች፣ በተመሳሳይ ተጀምሯል፤ ኢትዮ ቴሌኮም ጎን ለጎን እየሰራ ነው። በስማርት ከተማነት በኢትዮጵያ በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀሰው አዳማ ናት። አዳማ ላይ የኢንተርኔት ሲስተምን በመዘርጋት በማናጅመንት ላይ፣ በገቢ አሰባሰብ ላይ፣ በመሬት አስተዳደር ላይ ተጀምሯል። አዳማ ላይ መሬት በካዳስተር አሰራር በተቀናጀ መልኩ ወደ መተግበር ተገብቷል። በአዲስ አበባም ላይ ተጀምሯል፣ ባህርዳር፣ ሀዋሳ ከተሞችም ጅማሮዎች አሉ። ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ከማድረግ አኳያም የአመራር ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ነው።

ሰው ተኮር የሆኑ ከተሞችን ለመፍጠር ቀን እና ለሊት መስራቱ ተገቢ ነው። በሙያቸው የተካኑትን በማሰማራት ከተሞቻችን ለዘላቂ ልማት እንዲበቁ በተባበሩት መንግሥታት የተቀመጠውን የሚሊኒየሙ የዘላቂ ልማት ግብ 11 መሰረት በመንግሥታትም በሀገራችን ተግባራዊ እየተደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- አዲስ አበባ ከተማ እንደ ሀገሪቱ ርእሰ መዲናነቷ፣ እንደ አፍሪካ ህብረትና ሌሎች**



**ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ተቋማት መቀመጫነቷ በእዚህ ደረጃ ካሉ ከተሞች አኳያ በምን ደረጃ ላይ ትገኛለች ይላሉ? የሚጎድላት ብዙ ነው ካሉ እንዴት አርጋ መሙላት ትችላለች?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል፡-** አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት ዋና ከተማ፣ የተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ከተማ መሆኗ ከሌሎች ከተሞች ልዩ ባህሪ እንዲኖራት አድርሎጓል። በዓለም ካሉት አራት ከተሞች አንዷ የዲፕሎማቲክ ከተማም ናት። ይሄ ሁሉ ትሩፋት እያላት ከዚህ ሁሉ መጠቀም የሚያስችላትን ደረጃ ሳታሟላ ቆይታለች። ይሄንን ግምት ውስጥ በማስገባት አዲስ አበባ ዳግም እየለማች ነው። አሁን ለሌሎችም ጥሩ ምሳሌ በምትሆንበት ደረጃ ላይ ትገኛለች።

ከተማዋ የፕላን ጉድለት አለባት። ፕላኑን የማስተግበር ጉድለትም አለ። ወደ ሀገሪቱ ሌሎች ከተሞች በሚኬድበት ጊዜም ፕላን ይዘጋጃል፤ ነገር ግን መሬት ወርዶ ተፈፃሚ አይሆንም። አንዳንዱ ፕላን ደግሞ ያለጊዜ ይመጣል። ከተሜነትን መምራት እንጂ ማቆም አይቻልም። ከተማን በእቅድ እና በፕላን በመምራት የ10፣ የ20፣ የ30 ዓመታት በቂ የኃይል እና የውሃ አቅርቦት፣ በቂ ትምህርት ቤት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ጤና ተቋማት፣ የመናፈሻ እንዲሁም የልጆች መጫወቻ ስፍራዎች መገንባት ያስፈልጋል።

ከተሞችን ዳግም ማልማት የሚለው ሃሳብ የተጀመረው በእንግሊዝ ሀገር በተካሄደው የኢንዱስትሪ አብዮት ወቅት በተለይም በ1850 ዓ.ም ነው። በወቅቱ የኮሪደር ልማት ካስፈለገባቸው ምክንያቶች መካከል የፋብሪካ ምርትን በአግባቡ ማጓጓዝ፣ የአካባቢን ፅዳት ማስጠበቅ፣ የከተማ ውበት ማስጠበቅ የሚሉት ይገኙበታል።

በ1900 ዓ.ም አካባቢ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሲመሠረት ሚናስ የሚባል የመጀመሪያው አርመናዊ ማስተር አርክቴክት ከተማዋን በፕላን ለመሥራት ጥረቶች አድርጓል። በወቅቱ ሰፈሮችን የማፍረስ እንቅስቃሴዎችም ነበሩ። በጣሊያን ዳግም ወረራ ወቅትም እንዲሁ አዲስ አበባ የፈረንሳይ እና የጣሊያን አርክቴክቶች ሲፈራረቁባት ነበር።

እስከአሁን ባለው አካሄድ አዲስ አበባ በቂ ውሃ የላትም፤ የኃይል አቅርቦት እጥረትም ነበረባት። የጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ የመናፈሻ ስፍራዎች፣ የልጆች መናፈሻ ስፍራዎች እጥረት አለ። ይህንን ከግምት በማስገባትም አሁን በኮሪደር ልማቱ የእግረኛ መሄጃ ክፍት ስፍራዎች፣ የብስክሌት መሄጃዎች፣ በየቦታው ባሉ ኪስ ቦታዎች ዛፎችን በመትከል እና አረንጓዴ ስፍራዎችን የመፍጠር ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

መዲናዋን ዳግም የማልማት ጥያቄ የከተማ አስተዳደሩንና የፌዴራል መንግሥቱን አመራር ውሳኔና ቁርጠኝነትን የጠየቀ ነው። ከምሥረታዋ ችግር የነበረባት እና ያለ ፕላን ያደገችውን አዲስ አበባ የመጣችበትን አካሄድ ለመቀየር ውሳኔ በማሳለፍ ሕግና ሥርዓትን እንደገና በማሰብ ዳግም እየለማች ነው።

**ኮሪደር ልማቱ ሰው በነፃነት የሚንቀሳቀስበት፣ የሚኖርበት፣የሚዝናናበት፣ የቱሪዝም መስሕብ እና የውበት ከተማ እንዲሆን እና ዘላቂ የሆነ ልማትን ለማረጋገጥ የመጣ የልማት ሞዴል ነው**

ኮሪደር ልማቱ ሰው በነፃነት የሚንቀሳቀስበት፣ የሚኖርበት፣ የሚዝናናበት፣ የቱሪዝም መስሕብ እና የውበት ከተማ እንዲሆን እና ዘላቂ የሆነ ልማትን ለማረጋገጥ የመጣ የልማት ሞዴል ነው። ሞዴሉን በሌሎች ከተሞችም ላይ በተመሳሳይ በመተግበር ከተሞችን የልማት ማዕከላት ማድረግ ይገባል። ተገቢ የቤት አቅርቦት የተሟላባቸው ከተሞችንም ከመፍጠር አንጻር መንግሥት የፋይናንስ ተቋማትንም በማገናኘት እየሠራ ነው።

የዝናብ ውሃ ማስወገጃ መሰረተ ልማቶች በሚገባ ባለመኖራቸው በአንዳንድ አካባቢዎች ሁልጊዜ በጎርፍና ደራሽ ውሃ የመጠቃት ሁኔታዎች ይታያሉ። የመብራት፣ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ጨምሮ ሌሎችም ሰፋፊ ችግሮች ነበሩባት። እነዚህን ሁሉ ችግሮች በመለየት በዘርፍ ደረጃ የከተማ አስተዳደሩም ይሄንን በመስራት አሁን በግልጽ የታየውን ለውጥ እያመጣ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- በአዲስ አበባና በአንዳንድ የክልል ከተሞች በአሁኑ ወቅት እየተከናወነ የሚገኘው የኮርደር ልማቱ ከመሰረተ ልማት፣ ከጽዳት፣ ከተሜነትን ከማጎልበት አኳያ ምን ፋይዳ አለው?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ፡-** በመዲናዋ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የኮሪደር ልማቱ፣ ከተሞች እንዴት ውበታቸውን አጉልተው ማሳየት እንደሚችሉ ማሳያ ነው። አዲስ አበባ በኮሪደር ልማቱ በድጋሚ እየለማች ነው። ተገቢ የሆኑ የተሽከርካሪ መንገዶች፣ የእግረኛ መሄጃዎች፣ የፍሳሽ እና የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች፣ የንፁህ መጠጥ ውሃ መስመር፣ የመብራትና የቴሌ መስመሮች በሙሉ በተናበበ መልኩ እየተሠሩ ናቸው። ዘላቂ የሆነ የተቀናጀ የመሠረተ ልማት ፕላን እንዲመጣ አድርጓል። በኮሪደሩ በግራና ቀኝ ደግሞ ኪነ ሕንፃ ጥበባቸው የተጠበቀ የሚያምሩ ሕንፃዎች እንዲመጡ፣ ቅይጥ የሆነ እና በአንድ ሕንፃ ሁሉም አገልግሎት ያለበት ሞዴል ተግባራዊ መሆን ጀምረዋል። ቢሮ ያለበትና እዚያው የሚሠራበት፣ የሚነገድበት፣ የሚኖርበት የሚለው ሃሳብ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። የኮሪደር ልማት የከተማ ዲዛይን አንዱ ሞዴል ነው። ሌሎች ሀገራትም ይሄንን ተግባራዊ አድርገዋል።

በመዲናዋ ሰው በነፃነት የሚንቀሳቀስበት፣ የሚኖርበት፣ የሚዝናናበት፣ የቱሪዝም መስሕብ እና የውበት ከተማ እንዲሆን እና ዘላቂ የሆነ ልማትን ለማረጋገጥ የመጣ የልማት ሞዴል ነው። ከተማዋ አሁን ይበል በሚያሰኝ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ይሄንንም በማጠናከር ለሚቀጥለው ትውልድ ጭምር የመኖሪያ፣ የመነገጃ፣ የማምረቻ፣ የሥራ ፈጠራ፣ የቱሪዝም ማዕከል እንድትሆን ማድረግ ተገቢ ነው።በዚህ ረገድ የሚታዩት ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴዎች በክልል ከተሞችም ተጀምረዋል። ይህም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ይህ እንቅስቃሴ ወደ ሀዋሳ፣ ባህርዳር፣ ሻሸመኔ፣ መቀሌ፣ ጎንደር፣ ሆሳዕና፣ ሰዶ ከተሞች ሁሉ መስፋፋት መቻል አለበት። ወደ ክልል ከተሞችም እንዲሰፉ ማድረጉ ከተሞቻችን የስራ ፈጠራ ማዕከላት፣ የመናፈሻ ማዕከላት እንዲሆኑ የሚያግዝ ነው። ይህም የከተሞቻችንን ትሩፋት ማህበረሰቡ እንዲጠቀም ከማድረግ አንፃር የጎላ ሚና አለው። በመሆኑም ይሄንን አጠናክሮ መስራት የሚጠበቅ ነው። የሀገራችንን ልማት እድገት እና ብልፅግና ለማረጋገጥ በፕላን የተመሰረተ ከተሜነት ያስፈልገናል። የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ከክልል፣ ከዞን እና ከወረዳ መንግሥታት እና አስተዳደሮች ጋር በመሆን መስራት ይኖርበታል።

የኮሪደር ልማቱ እንቅስቃሴዎች ሕዝቡ ከከተሞቹ ትሩፋት እንዲጠቀም፣ ከተሞቹ እንዲያድጉ፣ የሥራ ፈጠራ ማዕከላት፣ የመናፈሻ ማዕከላት እንዲሆኑ ያግዛሉ። በሌሎች ከተሞችም ሁለተኛ ዋና ከተማ፣ ሦስተኛ ዋና ከተማ በሚል የቱሪዝም፣ የንግድ፣ የማምረቻ፣ የመናፈሻ ማዕከላት እንዲሆኑ የየራሳቸውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ፋሽን

## ቀርከሀን በፋሽን ኢንዱስትሪው የምታስተዋውቀው ዲዛይነር

**ሰሚራ በርሀ**

ቀርከሀን በመጠቀም በፋሽን ኢንዱስትሪው ላይ ተፈላጊ የሚባሉ ምርቶችን በማቅረብ ደንበኞችን አፍርታለች። ምርቱን በማስተዋወቅና በመጠቀም ለእናቶች እና ለወጣቶች የሥራ እድል መፍጠር የሚችል ‹‹ጤና አዳም›› የተሰኘ ተቋምም መስርታለች፡፡ የእደጥበብ ውጤቶች ዲዛይነርም ናት፡፡ ወይዘሮ ትዕግስት አበበ የጤናአዳም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት መስራችና ባለቤት ፡፡

ትዕግስት ከልጅነቷ ጀምሮ ለእደጥበብ ውጤቶች እና ለተፈጥሮ ቅርበት የነበራት ሲሆን፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ገብታ ከተመረቀች በኋላም ከተፈጥሮ ጋር የተቆራኘ የራሷን ስራ መስራት ትፈልግ ነበር፡፡ ትዕግስት ከዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ በኋላ በአየር መንገድ ውስጥ በበረራ አስተናጋጅነት ለዓመታት ሰርታለች፡፡ በዚህ አጋጣሚም ሌሎች ሀገራትን የማየት እድሉን አግኝታ ነበር፡፡

‹‹ወደ ተለያዩ ሀገራት ስበር ዜጎቻቸው ለተፈጥሮ ሀብቶቻቸው ያላቸው ቦታ እና አጠቃቀማቸው ያስቀናኝ ነበር›› የምትለው ወይዘሮ ትእግስት፤ ኢትዮጵያ በዓለም ላይ የምትጠራበት ያለቀላቸው ምርቶች አናሳ መሆን ቁጭት ይፈጥርባትና ያንንም ለመቀየር ትፈልግ እንደነበር ትገልጻለች፡፡

ሶስተኛ ልጇን ወልዳ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለም ላይ ተስፋፍቶ ስጋት መሆኑ በታወጀበት ወቅት በቤት ውስጥ መቀመጥ የግድ ሲሆን ትዕግስት ከተፈጥሮ ጋር የተገናኘ ምርት ማሰብ ጀመረች፡፡ ‹‹ምን ላይ ብሰራ ይሻላል? የሚለውን ጥናት ሳደርግ ጥሩ ሆኖ ያገኘሁት የቀርከሀ ምርትን ነበር›› የምትለው ወይዘሮ ትእግስት፤ አሁን አሁን የተጠቃሚው ፍላጎት ከተፈጥሮ ይልቅ በፕላስቲክ ከተሰሩ ምርቶች ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ትገልጻለች።

ይህ ልምድ ደግሞ ምርቶችን ተገልግሎ ለማስወገድ በሚሞከርበት ወቅት አካባቢን የሚበክል ስለሆነ የራሱ አደገኛ ጉዳት እንደሚያስከትል ትናገራለች። በዚህ ምክንያት በቀላሉ ማስወገድ በምንችላቸው አካባቢን የማይበክሉ ምርቶች ላይ ለማተኮር ወሰንኩ ስትል ታስረዳለች።

ከዚህ ውሳኔዋ በኋላ ነው ትእግስት ቀርከሀን በፋሽን ኢንዱስትሪው ለመጠቀም ጥናት በማድረግ ስልጠናውን በመውሰድ ስራውን የጀመረችው። ሆኖም ግን ወደ ተግባር ስትገባ ቀርከሀውን ወደ ምርት የምትቀይርበት መሳሪያ ከፍተኛ ድምፅ ስላለው ያንን ማስወገድ የሚያስችል ምቹ ቦታ ለማግኘት ተቸገረች። ስራውን ማቋረጥ መፍትሄ ስለማይሆን ቀጠለችበት።



‹‹በቅድሚያ የጀመርኩት በማበጠርያ ነበር፤ ከዚያ በምሰራበት ወቅት ሌሎች ዲዛይኖች እየመጡልኝ ቦርሳ የእጅ ብራስሌት፣ ቀለበት የአንገትና የጆሮ ጌጥ መስራት ቀጠልኩ›› የምትለው ወይዘሮ ትእግስት፤ በአሁኑ ሰዓትም ቀርከሀን እንደ ዋና ግብዓት በመጠቀም እና ከሌሎች የሀገራችን ሀብቶች ጋር በማጣመር የእደጥበብ ውጤቶችን ጌጣጌጦችን እና ቦርሳዎችን በመስራት ለገበያ እንደምታቀርብ ታስረዳለች። ከተለያዩ ሆቴሎች ጋር በጋራ በመሆን የድርጅታቸውን ብራንድ እና ሌሎች መገልገያዎችን ትሰራለች፡፡

እንደ ወይዘሮ ትእግስት ማብራሪያ፤ ቀርቀሀ በሀገራችን በስፋት የሚገኝ ሲሆን፤ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ለምግብነትም ጭምር ይውላል፡፡ በመሆኑም በጤናአዳም የሚሰሩ እነዚህ የቀርቀሀ ውጤቶች በተቻለ መጠን የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች ሙለሙሉ በሀገር ውስጥ የሚገኙ ብቻ እንዲሆኑ ይፈለጋል፡፡ በዚህም ጌጣጌጦችን ለመስራት የሚጠቀሟቸው ሌሎች ብረት ነሀስና መዳብ ሲሆን፤ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ናቸው። ምንም አይነት የጎንዮሽ ጉዳት የላቸውም። በጆሮም ሆነ አንገት ላይ የሚደረጉ ጌጦችም ክብደት የሌላቸው በመሆናቸው ምቹ ያደርጋቸዋል፡፡ ከቀርከሀ የሚሰሩ ቦርሳዎችም ከቆዳ፣ ፈትል እና ከባህል አልባሳት ጋር በማጣመር ይሰራሉ፡፡

ወይዘሮ ትእግስት እንደምትለው፤ ጌጣጌጦችንም ሆነ ቦርሳዎችን ዲዛይኖች ከሀሳብ በመነሳት የምትፈጥራቸው ሲሆን፤ የራሳቸው የሆነ መልዕክትን እንዲያስተላልፉም ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በተለያየ መጠንና ዲዛይን የሚሰሩ ሲሆን ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት የየራሳቸው ስያሜ ይሰጣቸዋል።

‹‹አንድ አዲስ ዲዛይን ሰርተን እንዳወጣን ስም ስላላወጣንለት ምርቱን የገዛችንን የደንበኛችን ስም በመጠቀም ‹ንባቤ› ብለን ሰየምነው›› በማለት የምትገልጸው ወይዘሮ ትዕግስት፤ ሌሎች ምርቶቻቸውም ምጥን ፣ ዘወትር (ሁል ጊዜ ሊያዝ የሚችል ቦርሳ ሲሆን) ኩሩ፣ እንዲሁም በእንስቶች ስም ውቢት፣ የውብዳር፣ ዝናሽ የሚሉ ስያሜዎችን እንደሰጧቸው ትናገራለች። በተለይ ለየት ያሉ የቦርሳ ስያሜዎች መኖራቸውን ገልጸ፤ በተለምዶው ዋሌት ተብሎ የሚጠራውን ገንዘባቸውን በመቀነታቸው ይይዙ የነበሩ እናቶችን ለማስታወስ በማሰብ መቀነት የሚል ስያሜ እንደሰጡት ትገልጻለች፡፡

እንደ ወይዘሮ ትእግስት ገለጻ በተለይ ከቀርከሀ ምርት የተሰሩትን ቦርሳዎች ተጠቃሚዎች ወደ ስራ ሲሄዱ፤ ጉዞ በሚኖራቸው ጊዜ፣ ስፖርት ቤት መሄድ ሲፈልጉ፣ ኮምፒውተር መያዝ ሲፈልጉ በቀላሉ ሊጠቀሟቸው ይችላሉ። ቦርሳዎቹ ከቀርከሀ ባሻገር ቆዳን እንዲሁም በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ የባህል አልባሳትን በማጣመር የሚሰሩ ናቸው፡፡ እነዚህ የቀርከሀ ውጤቶች በሰዎች ዘንድ ባህላዊ እይታ መጨመር ብቻ ሳይሆን ዘመናዊ የሆነ ይዘት የተላበሱና ለፋሽን ተጠቃሚዎች ምቹ ናቸው፡፡

‹‹ቀርከሀ በባህሪው እንደሌሎች እንጨቶች አይሰበርም ፤ተጣጣፊ ነው ፤ስንሰራውም ደግሞ በጣም ተልጎ በከፍተኛ ጥራት ነው›› የምትለው ዲዛይነሯ፤ ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች ቦርሳዎቹ ባላቸው ውበት አድናቆት ቢኖራቸውም ከቀርከሀ የተሰሩ መሆናቸውን ሲያውቁ ጥንካሬው ላይ ጥርጣሬ እንደሚያሳድርባቸው ትናገራለች፡፡

የጥንካሬና ጥራት ጉዳይም ሊያሳስባቸው እንደማይገባ ትመክራለች። እነዚህን ስራዎች የሚሰሩ እናቶችን ጊዜ ወስደው እንደሚያሰለጥኑም ታነሳለች፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜም 20 የሚሆኑ እናቶችን በዚህ ዘርፍ በማሰልጠን ራሳቸው ቀርከሀውን ተረክበው በሚፈለገው መንገድ ሰርተው እንዳስረከቡ ታነሳለች፡፡

ዲዛይነር ትዕግስት ሰዎች አሁን ላይ ያላቸው አቀባበል መልካም የሚባል መሆኑን አንስታ፤ እንደ ሀገር ባለን ሀብት ልክ ዘርፉ ይበልጥ መተዋወቅ አለበት ትላለች። አምራቾች፣ ባለሙያዎች፣ ወጣቶች ዲዛይነሮችም በዚህ ስራ ላይ እንዲገቡ ትጋብዛለች፡፡

‹‹ጤናአዳም›› አሁን ከሚሰራቸው ስራዎች ባለፈ ቀርከሀን በመጠቀም የሚሰሩ የውበት መጠበቂያ ምርቶችን የማምረት እቅድ አለው። ዲዛይነሯ ወደፊት ቀርከሀ ከሚያድግበት መንገድ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ውጤት ድረስ ሰዎች ጎብኝተው ራሳቸው የሚፈልጉትን አይነት ጌጣጌጥ አዝዘው የሚሄዱበትን መንደር የመገንባት ፍላጎት አላት፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## እነ ሰበቡ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

አበው ሲተርቱ ‹‹ክፉ ቀን አይምጣ›› ይላሉ፡፡ይህን ያሉት ደግሞ ያለምክንያት አይደለም፡፡በክፉ ቀናት ክፉ የሚባሉ ሰዎች ቢገጥሟቸው እንጂ፡፡ አንዳንዴ በገጠመኝ የሚከሰቱ እውነታዎች ይህን ተረት ደጋግመን እንድናስታውሰው ያስገድዱናል፡፡ አጋጣሚዎቹ እንደ ቃሉ ይዘት ክፉ የሚባል ደረጃ ባያሰጣቸውም ሁኔታዎች ግን ከእዚሁ ሀቅ እንዳንርቅ ያደርጉናል፡፡

የሰሞኑ እውነታ ደግሞ ለዚህ የአበው አባባል ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡ እንደሚታወቀው አሁን ላይ በሀገራችን የዶላር ምንዛሪ ዋጋ መጨመሩ ይታወቃል፡፡ እንዲህ መሆኑ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ላይ የራሱ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ግልፅ ነው፡፡

አጋጣሚው ሰበብ የሆነላቸው አንዳንዶች ደግሞ ድርጊታቸው ከታሰበው በላይ ሆኗል፡፡ ከሰሞኑ በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀናት ‹‹ሸው›› ማለት የጀመረው መረጃ እንደተራ ነገር የናኘ አልነበረም፡፡ እንዲህ መሰሉን ወዝ ያለው ወሬ ነቅተው የሚጠብቁ ስግብግቦች አጋጣሚውን በደስታ ተጠቅመውበታል፡፡አሁን ላይ በበርካታ አካባቢዎች የሸቀጦች ዋጋ ሰማይ መንካት ጀምሯል፡ጥቂት የማይባሉ ነጋዴዎች ሱቆቻቸው ከመሸጫነት ተሻግረው የማከማቻ መደብሮች እየሆኑ ነው፡፡

ትናንት ከሚታወቀው ዋጋ በተጋነነ መልኩ የሚጨምሩ ሸቃጮች ባሉበት ብቻ የሚቆዩ አልሆኑም፡፡ ማግስቱን ሌላ ዋጋ ጨምረው በአዲስ ሂሳብ ይደራደራሉ፡፡ በጉዳዩ ተገርሞ ስለምን የሚል ከተገኘ ደግሞ ማብራሪያ አያጡም፡፡ሰበባቸው ሁሉ የሰሞኑ የዶላር ምንዛሪ ጉዳይ ይሆናል፡፡

ብዙ ነዋሪዎች በሁኔታዎች ተማረዋል፡፡ ደንግጠዋልም፡፡ ዛሬ ያለአንዳች መነሻ አንዷ እንቁላል በአስራአምስት ብር ከተሸጠች ነገ ህይወት በምን መልኩ ሊቀጥል እንደሚችል መገመት አያቅታቸውምና፡፡

መሰረታዊ በሚባሉ የምግብ ፍጆታዎች ላይ የተጋነነ ዋጋ ለመጨመር የተዘጋጁ ስግብግቦች ከሰሞኑ ስራ በዝቶባቸዋል፡፡ ሱቆቻቸውን እያሰፉ፣ቦታ እያደላደሉ ነው፡፡ ቀድሞ በተገቢው ዋጋ የገዙትን ዕቃ ደብቀው ለማቆየት እንቅልፍ ካጡ ከራርመዋል፡፡ተፈላጊ ዕቃዎችን በተጠየቁ ጊዜም አንደበታቸው ‹‹የለም›› ለማለት የፈጠነ ነው ፡፡ አያገባቸው ገብተው የየዕለቱን የባንኮች የዶላር ዝውውር ማየት የጀመሩም አልታጡም፡፡ በአንድ ኪሎ ምስርና ሩዝ ላይ ዋጋ ለማከል የዶላር ዋጋውን ከፍታ ለማየት ሲሽቀዳደሙ ሀፍረት ይሉትን አያውቁም፡፡

ከሰሞኑ የዘይት፣የምስር የሩዝ ፣ፓስታና ማካሮኒ ዋጋ ከወትሮው ማሻቀብ በተለየ ምክንያት አይደለም፡፡እነዚህን ምርቶች ጨምሮ ሌሎች ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦች ሰበባቸው የዶላር ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡ይህ ክፋት የሞላበት የግብይት ልማድም በየአጋጣሚው ሲከሰት ተስተውሏል፡፡

ዋጋ ባሻቀበ ነውርነት በሰፋ ቁጥር እንዲህ እንደ አሁኑ የሚመለከታቸው አካላት የነጋዴዎቹን ሱቅ ከጥብቅ ማሳሰቢያ ጋር እያሸጉ፣ ያሳዩናል፡፡ ወቅቱን የመጠነ ዜና ተሰርቶም ወሬው ሲናፈስ ይቆያል፡፡ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ግን እሽግ ሱቆች ተከፍተው መደበኛ ስራቸው ይቀጥላል፡፡

አስገራሚው ጉዳይ ይህ መሆኑ ብቻ አይደለም፡ ፡ ነጋዴዎቹ በራሳቸው ይሁንታ ሰማይ ያጎኑት የገበያ ዋጋ አንዳች ለውጥ ሳይኖረው በጅምሩ ይቀጥላል፡፡ አሸገናል፣ አስጠንቅቀናል የሚሉ አካላት ሳይቀር በግብይቱ ያመኑበት ይመስል ጣልቃ ገብነታቸው ከስም እንጂ ጎልቶ አይታይም፡፡በዚህ ሁሉ መሀል ተጎጂ ሆኖ የሚቀረው ታዲያ ሸማቹ ህብረተሰብ ብቻ ይሆናል፡፡ተጠቃሚው በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚደርስበት የኑሮ ውድነት አቅሙ ይዳከማል፡፡ የኢኮኖሚው ጫና ቀና ብሎ እንዳይሄድ ሰበብ ነውና ለድህነት እጁን ሲሰጥ አይዘገይም፡፡

አብዛኛው ነዋሪ አሁን ላይ በፊታኝ የኑሮ ስጋት ተሸብቧል፡፡ ገና ከጅማሬው ይህ ምልክት መስተዋሉም የነገውን ችግር አስቀድሞ እንዲተነብይ ምክንያት እየሆነ ነው፡ ፡ ብዙ ጊዜ እንዳሻቸው በሚሆኑ ነጋዴዎች ላይ የሚወሰደው ርምጃ መላላቱ ድርጊቱን በስፋት እንዲደጋግሙት ድፍረት ሆኗቸዋል፡፡

እርግጥ ነው ከሰሞኑም በተስተዋለው ሙከራ የአንዳንዶች ሱቅ መታሸጉን ሰምተናል፡፡የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በሰጠው መግለጫም ዶላር ጨመረ በሚል ሰበብ የዋጋ ንረት በታየባቸው 77 የንግድ ድርጅቶች ላይ ሕጋዊ ርምጃ ተወስዷል፡፡ ይህ ብቻውን ግን ስር ለሰደደው አሳሳቢ ችግር በቂ ሆኖ አይገኝም፡፡ ቀጥሎ በሚሆነው ፈጣን መፍትሄ ላይ ተጠቃሚው መልስን ይሻል፡፡

ምንጊዜም ቢሆን ሸማቹ ከኑሮው ጋር የሚመጥን የዋጋ አቅርቦት ያስፈልገዋል፡፡ ጊዜና አጋጣሚን አሳበው ህይወቱን የሚያከብዱበት ስግብግቦችም በሕግ ቢጠየቁለት አይጠላም፡፡ ይህ እውነታ በአግባቡ ያለመተርጎሙ በቀጥታ ተጠቃሚውን ሲጎዳው ቆይቷል፡፡

እስካሁን የነበረው የአገም ጠቀም ርምጃ ለሕገወጦች መበራከት ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ተጠቃሚው ስጋት ቢያድርበት አይፈረድም፡፡ እውነቱን ለመነጋገር አጋጣሚና ሰበብ እየፈለጉ ነዋሪውን በኑሮ ውድነት የሚፈትኑ ስግብግቦች አስተማሪ የሚባል ርምጃ ሲያገኛቸው አይስተዋልም፡፡እንዲያ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ላይ ብድግ ብለው በማን አለብኝነት ገበያውን አይዳፈሩም፤ በነዋሪው አቅም አይቀልዱም ነበር፡፡

ማንምእንደሚረዳው ያለአንዳች በቂአቅርቦት የነጋዴዎች ጎተራ አይሞላም፡፡ተጠቃሚው በሌለበት አግባብም የሻጭ ለዋጩ ህልውና አይቀጥልም፡፡ይህ እውነት ግልጽ ቢሆንም አንዳች አጋጣሚ በተፈጠረ ቁጥር ስግብግቦቹ ነጋዴዎች ትስስሩን ይዘነጉታል፡፡ ታምኖ የሚገዛቸውን ተጠቃሚ ገሸሽ አድርገውም ለራስ ጥቅም ብቻ ይሮጣሉ፡፡አሁንም መንግሥት ሱቆችን ከማሸግና ማስጠንቀቂያ ከመስጠት የዘለለ ርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ እንደዋዛ ተሰቅሎ የሚቀረውን የገበያ ዋጋ በነበረበት ከቀጠለ ግን ሀገር ትጎዳለች፡፡ ኢኮኖሚው ለአንድ ወገን አመዝኖም ኑሮ ፍትሀዊነትን ይነጠቃል፡፡

ብዙዎች እንደሚሉት ዛሬ ላይ እየተስተዋለ ላለው የኑሮ ውድነት መንግሥት የራሱን አማራጭ መውሰድ ይኖርበታል፡ ፡ ገበያውን በሚደጉሙና ኑሮን በሚያረጋጉ ስልቶች መንቀሳቀስ ካልተቻለ የኑሮ ክብደት ጫናው አይቀልም፡፡ አጋጣሚን እየጠበቁ ከሕግ በላይ የሚሆኑ ሕገወጦች በአግባቡ ካልተዳኙ ህይወት ሚዛናዊ አይሆንም፡፡

አሳሳቢውን የምግብ ፍጆታ ጉዳይ እንደመነሻ አወሳነው እንጂ ችግሩ በዚህ ብቻ የሚበቃ አይደለም፡፡ አሁን ላይ ዶላርን አሳበው ንግድን የሚከውኑ አካላት በእጆቻቸው የሚገኙ ማናቸውንም ዕቃዎች በእጥፍ ለመጨመር የሚያግዳቸው አይኖርም፡፡ በተለይ ዕቃዎችን ከውጭ ሀገራት እናስገባለን የሚሉ ወገኖች አፋቸውን ሞልተው ለመናገር አጋጣሚው የሚያግዛቸው ይሆናል፡፡

እነሱን እንደ መነሻ ተከተልን የሚሉ አንዳንዶች ደግሞ የጉልት ፍጆታዎችን ዋጋ ጭምር ከዶላር ጋር ሊያዛምዱ የፈጠኑ ናቸው፡፡ ጉዳዩ በወጉ ያልገባቸው ወገኖች ሳይቀሩ በአጋጣሚ ራስን ለማክበር የሚያደርጉት ሩጫም ከመተዛዘብ ያለፈ ነው፡፡

አግባብነት ያለው የንግድ ሥርዓት ሰፍኖ ሁሉም እንደአቅሙና እንደፍላጎቱ ያድር ዘንድ ሕጋዊነት በወጉ ሊተገበር ይገባል፡፡ኮሽ ባለ ቁጥር ሰበብና አጋጣሚን አስልተው ለመቅደም የሚሮጡ ራስ ወዳዶችም ትርጉም ባለው ሕግ ሊዳኙ ግድ ይላል፡፡

ሀገር የምታድገው፣ኢኮኖሚ የሚልቀው ጥቂቶች በራስ ወዳድነት በልጠው ስለሄዱ አይደለም፡፡ በመተሳሰብ፣በመግባባት የሚዘልቁት ህይወት ፍሬያማ ሲሆን ሁሉም በአቅሙ፣በልኩ የመኖር ዕድል ያገኛል፡፡ለእንደኛ አይነቷ ሀገር የሚበጀው ደግሞ በመተሳሰብ ማደር ሲቻል ብቻ ነው፡፡

አሁንም ጊዜና አጋጣሚን እየጠበቁ ኑሮን በሚያከብዱ ራስወዳዶች ላይ ትርጉም ያለው ሕጋዊ ርምጃ ሊቀጥል ይገባል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለሕገወጦቹ ድርጊት ተባባሪ በመሆን ራሳቸውን በሙስና ድርጊት ዘፍቀው ያሉ አንዳንድ አካላት ጭምር በተለየ ዓይን ሊቃኙ ግድ ነው፡፡ ይህ እውነት በግልፅ የሚታይ ሀቅ ነውና፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ወታደራዊ ግዳጅ ያበረታቸው የፈረንሳይ ወታደሮች የፓሪስ ኦሊምፒክ ጥበቃውን ተያይዘውታል

የፓሪስ ኢሊምፒክ የተጀመረው ከጥቂት ቀናት በፊት ነው። ፈረንሳይ ከወዲሁ በባቡር መሥመሮቿ እና በኢንተርኔት አገልግሎቷ ላይ ጥቃት አስተናግዳለች። ቢሆንም በብዙ አስር ሺዎች የሚቆጠሩ ፖሊሶች እና የጦር ሠራዊት ወታደሮች ፀጥታ እንዲያስከብሩ አሰማርታለች።

በሰሜን ምሥራቃዊው የፓሪስ አካባቢ ለመዲናዋ የፀጥታ ጥበቃ የተመደቡት ፖሊሶች እና ወታደሮች በጠዋቱ እየተዘዋወሩ ጥበቃውን ተያይዘውታል። አብዛኛው የፓሪስ ነዋሪ ለበጋ የዕረፍት ጊዜው ሊዝናና ወደተለያየ ቦታ ሄዷል። የወትሮ ኅብኚዎችም የሉም። ቢሆንም ወታደሮች ከተማዋን በንቃት እየጠበቁ ናቸው። ሳጂን ያን የአንዱ የጥበቃ ቡድን አለቃ ሲሆን ለማንኛውም ለሚከሰት ነገር ዝግጁ ሆነን በንቃት እንጠብቃለን። አንዳች የሚያሰጋ ነገር ቢከሰት አለን። ነዋሪዎች ችግር አጋጥሟቸው ከፈለጉንም እንገኛለን” ብሏል።




ወታደሮቹ በፓሪስ ዙሪያ በተለያዩ ቦታዎች ሰፍረዋል። እነዚህ የአየር ወለድ ወታደሮች ከኢራቅ ወይም ከሳህል አካባቢ ሀገሮች ግዳጃቸው ላይ ተጠርተው የመጡ ሲሆኑ አንዳንዶቹም ግዳጃቸው ያጠናቀቁም አሉባቸው። ዋና ሳጂን ቻርሊ ጋቦን፡ ማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ አይቮሪኮስት እና ማሊ አገልግሏል። የማሊ ቆይታው አስቸጋሪ እንደነበረ ይናገራል። ሦስት ወር ሙሉ ያለማቋረጥ በፀረ ሽብርተኛ ተልዕኮ ማሊን ኒዠርን እና ቡርኪና ፋሶን በሚያዋስነው በረሃማ የድንበር አካባቢ አሳልፏል።

ወታደሮቹ ከንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት የጀመሩ እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰዓት ጥበቃ ላይ ናቸው። “ብዙ ሕዝብ ስላለ መጠበቅ አለብን። የባቡር ጣቢያው፣ ሴን ወንዝ፣ የኦሊምፒክ ታዳሚዎች ያሉበት ቦታ ሁሉም መጠበቅ አለበት” ብሏል ዋና ሳጂን ቻርሊ። ሻምበል ኮሬንቲን “ኦሊምፒክስ ጥበቃ ላይ በመመደቤ በጣም ኩራት ይሰማኛል። ፓሪስ ኦሊምፒክ ካስተናገደች ወደ 100 ዓመታት ተቆጥረዋል። ስለዚህ በሕይወት አንድ ጊዜ የሚያጋጥም ነገር ነው” ብሏል።

## ኢራን እሥራኤልን ማስፈራራቷን ተከትሎ አሜሪካ ተዋጊ ጄቶች እና የጦር መርከቦች ልታሰማራ ነው

አሜሪካ እሥራኤልን ከኢራን እና አጋሮቿ ከሚደርስ ጥቃት ለመከላከል በሚል ተጨማሪ የጦር መርከቦችን እና ተዋጊ ጄቶችን ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እንደምታሰማራ ፔንታጎን ገለጸ። በቅርቡ የሐማስ የፖለቲካ መሪ ኢስማኤል ሃኒያ በኢራን እንዲሁም የሊባኖስ ታጣቂ ቡድን ሄዝቦላ ከፍተኛ አዛዥ መገደላቸውን ተከትሎ በቀጣናው ውጥረት ነግሷል።

በመካከለኛው ምሥራቅ የሚሳኤል መከላከያ ኃይል ለማሰማራት ዝግጅት መጠናቀቁን የገለጸው ፔንታጎን እሥራኤልን ለመከላከል “የማያወላውል ቁርጠኝነት” አለ ብሏል። የኢራን መንፈሳዊ መሪ አያቶላ አሊ ኻሚኒ እሥራኤል በሃኒያ ግድያ “ከባድ ቅጣት” እንደሚጠብቃት ቃል ገብተው በአገሪቱ የሦስት ቀናት ብሔራዊ ኀዘን አውጀዋል።

የሐማሱ መሪ ኢስማኤል ሃኒያ ማክሰኞ ሌሊት ሐምሌ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ስምንት ሰዓት ላይ በኢራኗ መዲና ቴህራን ቤት ውስጥ ሳሉ ተገድለዋል። ኢራን እና ሐማስ መሪውን በሚሳኤል ጥቃት የገደለቻቸው እሥራኤል ናት ቢሉም እሥራኤል ይፋዊ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥባለች።

በጋዛ የተኩስ አቁም ድርድር ላይ ትልቅ ሚና የነበራቸው የ62 ዓመቱ ሃኒያ በቴህራን የኢራን ፕሬዚዳንት ማስዑድ ፔዜሽኪያን በዓለ ሲመት ላይ ከታደሙ ከሰዓታት በኋላ ነው የተገደሉት። የሃኒያ መገደል የተሰማው እሥራኤል የሄዝቦላህ ከፍተኛ አዛዥ የሆነውን ፉአድ ሹክርን መግደሏን ባሳወቀች በሰዓታት ውስጥ ነው።

# ሰላምና ኢኮኖሚ ለስኬታማ ዲፕሎማሲ

ታሪኩ ዘለቀ

ኢትዮጵያ ከ85 በመቶ በላይ በክረምት ወቅት ደግሞ ከ86 በመቶ በላይ ለዓባይ ውሃ አስተዋፅኦ ታበረክታለች። ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ በዓባይ ውሃ አንዳችም ጥቅም አልተጠቀመችም። ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የህዳሴ ግድብን ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ለመገንባት ስትነሳ ጫጫታው በርክቶ ነበር። አሁንም ድረስ በዚች ሀገር ላይ በእጅ አዙር ጭምር ጦርነቶች፣ግጭቶች፣አለመረጋጋቶች እንዲሰፍኑ ማድረግና ግድቡ እንዳይሞላ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ ደባና ተንኮል ሲያሴሩ እንደነበር ይታወቃል።

92 ከመቶ የውሃ ሀብቷ ወሰን እየተሻገረ እንጥፍጣፊዋን ከጎረቤቶቿ የማታገኘው ኢትዮጵያ ስለጋራ ተጠቃሚነት ከማንም ቀድማ ወትዋች ናት። የታላቁ ህዳሴ ግድብን ጉባ ላይ መገንባት ስትጀምርም ይህን የዘመናት የትብብር ቀናይነቷን አሳይታለች። በወንዞቿ ለመጠቀምና ድህነትን ለማስወገድ በምታደርገው ጥረት ሁሉ ራሷን ብሎም ጎረቤቶቿን ጭምር ለመጥቀም እንጂ ማንንም ለመጉዳት አለመሆኑን በተደጋጋሚ አሳውቃለች።

ኢትዮጵያ ህዳሴዋን እውን ለማድረግ ግድብ ለመገንባት ስትጀምር ለጋራ ተጠቃሚነት ጆሮዳባ ልበስ ብላ የቆየችው ግብፅ አራስ ነብር ሆና ብቅ አለች። መጀመሪያ መረጃ ስጡኝ በኋላ በገለልተኛ ቡድን ካልተጠና ከዚያም በሶስተኛ ወገን እንደራደር እያለች ካንጋሮአዊ አቋሟን ተያያዘችው። ኢትዮጵያ ግን የማይናወጥ አቋሟን በመሀላ ጭምር ገልፃ ግንባታዋን ቀጠለች እንጂ ለእንካሰላንቲያው ቦታ አልሰጠችም።

የዓለም አቀፍ የባለሙያዎች ቡድንም ሆነ የሶስቱ ሀገራት የቴክኒክ ቡድን ያቀረቡት ሪፖርት ለካይሮ ሹማምንት የሚዋጡ አልነበሩም። በመሪዎች ደረጃ የተደረጉ ውይይቶችም አጥጋቢ አልሆነላቸውም። እናም በገለልተኛ ሽፋን ሸሪኮቿን እንዲያደራድሯት አደራጀች፤ አሜሪካንና የዓለም ባንክን።

ኢትዮጵያ ግን ዋሽንግተንም ሆነች የዓለም ባንክ ከታዛቢነት ያለፈ ሚና አይኖራቸውም በሚል ለፊርማ ያቀረቡትን ሰነድ አልፈርምም ብላ ውድቅ አደረገችው። በወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕም ግብፅ ግድቡን ታጋየዋለች እስከማለት ደረሱ። ትራምፕ ባዶ ፉከራ የትም እንደማያደርስ ቢረዱም የተለመደ የአዞ ለቅሷቸውን ቀጠሉ።

የህዳሴው ግድብ ጉዳይ የፀጥታው ምክር ቤት አጀንዳ አድርጎ ሊይዘው ይገባል የሚል የውሃ ጉዳይን ተመልክቶ የማያውቀው የፀጥታው ምክር ቤት ይገላግለን ጥያቄአቸው ግን እንዳሻቸው አልሆነላቸውም። የኢትዮጵያ ልጆች እውነትን ይዘው አሸናፊ ሆኑ። ድል ጨብጠውም ስለትብብር እንጂ ሌላውን ስለመጉዳት አይናገሩም።

ኢትዮጵያ ስለጋራ እድገት ስትሰራ ግብፅ ግን ዜጎቿን በስጋት መወጠር ላይ ተጠምዳለች። መሪዎቿም ማስፈራሪያና እያንዳንዱን ነገር ከግድቡ ጋር የማገናኘት አባዜአቸው ለዘመናት ቅብብሎሽ የሚለወጥ አይመስልም።

ባለፉት አስራ ሁለት ዓመታት ወትሮውንም የተፈጥሮ ሀብቷ ብዙ ጠላት ያፈራላት ኢትዮጵያ በህዳሴው ግድብ ምክንያት በከባድ የዲፕሎማሲ ጫና ውስጥ ከርማለች። በፈተናም ውስጥ ሆና ትብብር ላይ ያተኮረችው ኢትዮጵያ የግድቡ ግንባታ እንደተጀመረ ሱዳንን ሁነኛ አጋር ለማድረግ ያደረገችው የዲፕሎማሲ ጥረት በፍሬአማነቱ ይነሳል። ሱዳን ይሁንታ ብቻ ሳይሆን በወቅቱ ፕሬዚዳንት የነበሩት አልበሽር ለኢትዮጵያ የ10 ሚሊዮን ዶላር የግንባታ ማሽነሪ በእርዳታ ሰጥተዋል። እርዳታውንም ሲያስረክቡ ከፈለጋችሁ ለህዳሴ ግድብም ተጠቀሙበት ብለው ነበር።

ግብፅ ከአረብ ሊግ እስከ አውሮፓ ህብረት፣ከአሜሪካ እስከ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሀሰት መረጃ አጋር ፍለጋ ስታማትር ኢትዮጵያ በአንፃሩ የግድቡ ግንባታ ማፋጠንን፣የውሀ ሙሌቱን ማስጀመርን መርጣለች። ሀቁ በሂደት ይገለጣል በሚልም ስራ ይቅደም ብላለች። ይሁን እንጂ ጫናውን የሚያቃልሉ እውነታን ለዓለም የሚነግሩ ዲፕሎማሲያዊ ስራዎችን መስራት ቀጥላበታለች።

> **ታላቁ ህዳሴ ግድብን ጉባ ላይ መገንባት ስትጀምርም ይህን የዘመናት የትብብር ቀናይነቷን አሳይታለች። በወንዞቿ ለመጠቀምና ድህነትን ለማስወገድ በምታደርገው ጥረት ሁሉ ራሷን ብሎም ጎረቤቶቿን ጭምር ለመጥቀም እንጂ ማንንም ለመጉዳት አለመሆኑን በተደጋጋሚ አሳውቃለች**

እንደዚህ ያሉ ጫናዎችን ኢትዮጵያ የምትቋቋመው ብቻዋን ሆና አይደለም። ከሌሎች ሀገራት ጋር አብራ መስራት ስትችል መሆኑን ቀድማ የተደራችው ኢትዮጵያ ትብብርንና የጋራ ተጠቃሚነትን አስቀድማለች። የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳየው ይህንኑ ነው። በዓለም ላይ ተሻጋሪ ወንዞችን የሚጠቀሙ ሀገራት በስምምነት በጋራና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ እየተጠቀሙ ቢሆንም የናይል ተፋሰስ ሀገራት ውሃውን በፍትሀዊነት እየተጠቀሙ አይደለም።

ይህ ኢፍትሀዊ አካሄድ ማብቃት አለበት በሚል የናይል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት እኤአ በ2006 የተዘጋጀ ሲሆን፤ የናይል ተፋሰስ ሀገራት የውሃ ሀብቶችን በትብብር ማልማትና ማስተዳደር የሚቻልባቸው ሁኔታዎችን ያስቀመጠ ነው። የናይል ተፋሰስ ኢንሼቲቭ /ኤን ቢ አይ የሽግግር ማዕቀፍ ሆኖ በዘጠኝ መስራች አባል ሀገራት የጋራ ራዕይ የተመሰረተና ቋሚ የናይል ወንዝ ተፋሰስ ኮሚሽን እስከሚመሰረት የሽግግር ማዕቀፍ ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ መቋቋሙ ይታወቃል።

ኢትዮጵያም የህዳሴ ግድብን በጀመረችበት ጊዜ የስምምነቱን ፊርማ አፅድቃለች። ሀገራት ስምምነቱን እንዳይፈርሙ ትልቅ ተፅዕኖ እንደነበረባቸው ይታወቃል። በገንዘብ ማባበያ፣ በማስፈራሪያ ምክንያት ጥቂት ሀገራት ብቻ ነበሩ ስምምነቱን የፈረሙት። በቅርቡ ደቡብ ሱዳን ስምምነቱን ፈርማለች። እንዲህ መሆኑ ትልቅ የዲፕሎማሲ ድል ነው።

በተለይ ደግሞ በውሃ አጠቃቀም ላይ ፍትሀዊነትን ለማስፈን ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ ድል ነው። የናይል ተፋሰስ ትብብር ማዕቀፍ በቅኝ ግዛት ዘመን የነበረውን እሳቤን በመያዝ በተለይ የታችኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት የትብብር ማዕቀፉን ለመፈረም አሻፈረኝ ብለው ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ከተፋሰሱ ሀገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ 50 በመቶ ያህሉ መፈረማቸው ለተሰራው ስራ ምላሽ የሚሰጥ ነው።

የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ በደቡብ ሱዳን መፅደቁ ስምምነቱ በተፋሰሱ ሀገራት ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን በቂ ድጋፍ አስገኝቷል። ረጅሙ የዓለማች ወንዝ የዓባይ ወንዝ አስራ አንድ የተፋሰስ ሀገራት ይጋሩታል። ሆኖም እስካሁን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በቀደመው ስምምነት ውሃውን ግብፅና ሱዳን ብቻ እንዲከፋፈሉት የሚል ነበር።

ታዲያ አዲሷ የተፋሰሱ ሀገር ደቡብ ሱዳን የወሰደችው እርምጃ ከጎረቤቷ ኢትዮጵያ ታሪካዊ ነው ተብሎለታል። ውሳኔው የቅኝ ግዛት ስምምነቶችን ለመሻርና በአዲስ ለመተካት የሚያስችለው የተፋሰሱ ሀገራት የትብብር ማዕቀፍ እውን እንዲሆን ያደርጋል። አዲሱ ስምምነት ከአስራ አንዱ ናይል ተፋሰስ ሀገራት መካከል ስድስት ሀገራት በፓርላማቸው ካፀደቁት ቋሚ የናይል ተፋሰስ ሀገራት ኮሚሽን ሙሉ በሙሉ ወደ ስራ መግባት ይችላል።

በተፋሰሱ ሀገራት መካከል ያለው ማዕቀፍ ምክንያታዊ፣ፍትሃዊ ሆኖ የናይልን ውሀ ለመጠቀም የሚረዳ ነው። ሀገራቱ ይህንን ተጠቅመው ማህበረሰባቸውን ለመጥቀም የሚያደርጉትን ጥረት ያግዛል። ደቡብ ሱዳን ስምምነቱን መፈረሟ ሀገራቱ የናይል ተፋሰስ ኮሚሽንን አቋቁመው በጋራ ሆነው ለማስተዳደርና ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚደረገውን ጉዞ ያፋጥናል። በሀገራቱ የሚኖረውን ጥምረት ያጠናክረዋል፤በተጨማሪም የናይል ተፋሰስ ማህበረሰብ የሚለውን ማንነት በቀጣናው ትስስር በመፍጠር ረገድ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

የናይል ተፋሰስ የውሀ ምንጭ የሆኑት የላይኛው የተፋሰሱ ሀገራት የትብብር ማዕቀፍ ስምምነቱ ፍትሀዊና ምክንያታዊ አጠቃቀም የሚለውን መርህ የሚያሟላ መሆን እንዳለበት በተደጋጋሚ ይገልፃሉ። ስምምነቱ የውሀ ደህንነታችን እና ታሪካዊ ድርሻችንን ማረጋገጥ አለበት የሚል አቋም ያላቸው ግብፅና ሱዳን ደግሞ እስካሁን ስምምነቱን አልፈረሙም።

የደቡብ ሱዳን ስድስተኛ ሀገር በመሆን ስምምነቱን ማፅደቅ ለኢትዮጵያም ሆነ ለቀጣናው ይዞት የሚመጣው እድል ከፍ ያለ ነው። ቀደም ሲል ኢትዮጵያን ጨምሮ አምስት ሀገራት ብቻ ነበሩ የፈረሙትና ያፀደቁት። ትጠበቅ የበረችው ስድስተኛዋ ሀገር ደቡብ ሱዳን አሁን አፅድቃለች። ይህ መሆኑ በተለይ ያልፈረሙ የላይኛው የተፋሰሱ ሀገራት ስምምነቱን ተቀብለው እንዲያፀድቁ የሚያበረታታ ነው። ፍትሀዊና እኩል ተጠቃሚነት የሚለው ሀሳብ ውሀውን በብቸኝነት የመጠቀም ዝንባሌ የነበረውን የቅኝ ግዛት ውል ተቀባይነት እንዳይኖረው ያደርጋል።

ደቡብ ሱዳን ለቀጣናው ጠቃሚ የሚባል ውሳኔ ከመወሰኗ በላይ ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ግንኙነት እንዲጨምር እድል ይፈጥራል። የተፋሰሱ ሀገራት ወደ ስምምነት ሲደርሱ በጋራ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ውሃውን መጠቀምና ማስተዳደር እንችላለን የሚል እምነት ይዳብራል። በተጨማሪም ደቡብ ሱዳን የናይል ስምምነት ማዕቀፍን መፈረሟ ለኢትዮጵያ ያላትን አጋርነትም ያሳያል። ይህም ኢትዮጵያ በተፋሰሱ ዙሪያ ያሉትን ሀገራት ፍትሀዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ተደጋጋሚ ጥረት ስታደርግ የነበረና ይህም ሃሳቧ ተቀባይነትና ድጋፍ እያገኘ ስለመምጣቱ አንዱ ማሳያ ነው።

ኢትዮጵያ ይህ እውን እንዲሆን ያደረገችው ጥረት አወንታዊ ዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ እያደረገች መሆኑ በውጤት የሚያሳይ ነው። ባለፉት ረጅም ዓመታት በዓባይ ወንዝ ተጠቃሚነት ዙሪያ ፍትሀዊነት እንዲመጣ ሚናዋ ላቅ ያለ ነበር። የናይል ስምምነትን ለማፅደቅ ሂደቱ ቀላል አልነበረም። ቢሆንም ኢትዮጵያ በኤምባሲዋ በኩል በተለይም ባለፉት ሶስት አመታት ብዙ ትግል አድርጋለች። በሰራችው ስራም ዲፕሎማሲያዊ ስኬት እየተቀናጀች ነው።

የዲፕሎማሲ ዋንኛ ዘዋሪው ግን ኢኮኖሚው ነውና ኢኮኖሚው መነቃቃት ሲጀምር በንቀትም ይሁን በርቀት ሲገፉን የነበሩ ሲመጡ እያየናቸው ነው። ያነሳነው ፍትሀዊ የወደብም ሆነ የውሀ ልማት ጥያቄ ቢያንስ ውሀውን በማንኪያ እንኳ መንካት አትችሉም ከሚል ድንፋታ ቀይ ባህር ላይ እድል፣ ፈንታ፣ ፅዋ፣ተርታ የላችሁም ከሚል ጫጫታም ተላቋል። የመልማት መብታችን ቢያንስ በመርህ ደረጃ ተቀባይነትን አግኝቷል።

ከዚህ የበለጠ አድገን ከእህል ልመና ብንላቀቅና ራሳችንን ብንችል ከዚህም ከፍ ብለን ለሌሎች ብንተርፍ ደግሞ የት እንደሚደርስ መጠበቅ ነው። ኢኮኖሚያችን እነዚህን እድሎች ካመጣልን በተለያዩ አካባቢዎች የሚታዩ ግጭቶችና ጦርነቶች፣ እገታዎችና የፀጥታ መደፍረሶች በሰላም ቢፈቱ፣መፈናቀሎች ቆመው ሁሉም ወደቀየው ቢመለስ ደግሞ ኢኮኖሚያችንም ዲፕሎማሲያችንም ጫፍ ላይ ወጥተው የመቀመጥ እድል አላቸው። እንደሕዝብ ከዚህ ዋነኛ ተጠቃሚዎቹ እኛው እስከሆንን ድረስ ሰላም እንዲሰፍን ዋነኛ ተዋናይ በመሆን ልንሰራ ይገባል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ታሪክ ቀያሪዎቹ እንቁዎች

ብርሃን ፈይሳ

የአሜሪካ፣ እንግሊዝ እና ኬንያ አትሌቶች ስኬታማ የሆኑበት የሴቶች 800 ሜትር ውድድር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዲስ ተፎካካሪ አግኝቷል። በተያዘው የውድድር ዓመት ግላስኮው ላይ በተካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮና ባልተጠበቀ ሁኔታ የወርቅ ሜዳሊያውን ያጠለቀችው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት በፓሪስ ኦሊምፒክም ክስተት ትሆናለች ተብሎ ይጠበቃል። ጥቁሯ እንቁ አትሌት ጽጌ ድጉማ ዛሬ ምሽት በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ታሪክ በርቀቱ የመጀመሪያውን ሜዳሊያ ለማስመዝገብ ትሮጣለች።

በመካከለኛና ረጅም ርቀት ውድድሮች ስኬታማ የሆነችው ኢትዮጵያ፤ በ800 ሜትር እአአ በ2013 በዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና መድረክ በአትሌት መሐመድ አማን የተገኘው የወርቅ ሜዳሊያ በታሪክ ቀዳሚው መሆኑ ይታወቃል። ተመሳሳይ ድል ለዓመታት ሳይደገም ቢቆይም በርቀቱ ኦሊምፒክን ጨምሮ በተለያዩ ሻምፒዮናዎች ላይ ተፎካካሪ በሆኑ አትሌቶች የዲፕሎማ ደረጃዎች ግን ተመዝግበዋል። በተያዘው የውድድር ዓመት መጀመሪያ ላይ በርቀቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁለተኛው ድል በወጣቷ አትሌት ጽጌ ድጉማ ግላስኮው ላይ በዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮና ሲመዘገብ ማንም አልጠበቀም ነበር። ዛሬ ምሽትም በፓሪሱ ኦሊምፒክ 800 ሜትር የኢትዮጵያ በዚህች ወጣት አትሌት ሜዳሊያ ታገኛለች ተብሎ ግምት ተሰጥቷታል።

ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተገኘችው የ23 ዓመቷ ወጣት አትሌት ጽጌ ድጉማ የጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ





**የዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮናዋ ጽጌ ድጉማና ወርቅነሽ መለስ በርቀቱ ታሪክ ፍፃሜ በመድረስ የመጀመሪያ ኢትዮጵያውያን ሆነዋል፣**

ማሠልጠኛ ተቋም ፍሬ እንዲሁም የንግድ ባንክ ክለብ አትሌት ናት። ሃገሯን እአአ በ2017 በአልጄሪያ አዘጋጅነት በተካሄደው ከ20 ዓመት በታች የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና በመወከል በ200 ሜትር የብር ሜዳሊያ ማጥለቅ ችላለች። በ400 ሜትር ደግሞ ከ2019 እስከ 2022 በተከታታይ በኢትዮጵያ ሻምፒዮና የሜዳሊያ ባለቤት በመሆን ቆይታለች። በ800 ሜትር ቀዳሚ ውድድሯን በቤልጂየም አድርጋ በአሸናፊነት ስታጠናቅቅ በቤልግሬድ የዓለም የቤት ውስጥ የዙር ውድድር 1ደቂቃ ከ59 ሰከንድ ከ66 ማይክሮ ሰከንድ በሆነ ፈጣን ሰዓት በመግባት ቀዳሚ እንደነበረች ይታወሳል። ልቃ በታየችበት የግላስኮው የቤት ውስጥ ዓለም ሻምፒዮናም ውድድሩን ተቆጣጥራ በመሮጥና የመጨረሻውን ዙር በፈጣን አሯሯጧ ልዩነት በመፍጠር 2:01.90 በመሆን ሰዓት በማሸነፍም ነው የወርቅ ሜዳሊያውን ያጠለቀችው።

የጽጌ ስኬት ከቤት ውጪ በተካሄዱ ውድድሮችም የተመሰከረ ሲሆን ጋና ላይ በተካሄደው የአፍሪካ ጨዋታዎች ላይ ለሃገሯ የወርቅ ሜዳሊያ አስገኝታለች። ሎስ አንጀለስ ላይ በተካሄደ ሌላ ውድድር ሁለተኛ ደረጃን ይዛ ብታጠናቅቅም የገባችበት 1:57.56 የሆነ ሰዓት ደግሞ በፍጥነቱ በቀዳሚነት ተመዝግቦላታል። አትሌቷ በኦስሎ እና ዩጂን ዳይመንድ ሊጎች በመሮጥም በውድድር ዓመቱ ከስኬት አልራቀችም። በወጣቱ አሠልጣኝ ዓለሙ ዋቅጅራ የምትሠለጥነው አዲስ ኮከብ ፓሪስ ላይ አንድ ነገር ትፈጥራለች የሚሉ ግምቶች ተበራክተዋል።

በትናንት ምሽቱ ግማሽ ፍፃሜ ማጣሪያ ሁለተኛ ሆና ስታጠናቅቅ የግሏን ፈጣን ሰዓት በ1:58:06 ማስመዝገብ ለዛሬው ፍፃሜ የደረሰችው ወርቅነሽ መለሰ ከተጠባቂ አትሌቶች አንዷ ስትሆን፣ ከፅጌ ዱጉማ ጋር በርቀቱ ታሪክ ለኢትዮጵያ ፍፃሜ መድረሳቸው በራሱ የተለዩ አድርጓቸዋል።

ከአራት ዓመት በፊት ቶኪዮ ኦሊምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀችውና በሌሎች ሻምፒዮናዎች ላይም በአስደናቂ አሯሯጧ የምትታወቀው የአሜሪካ ዜግነት ያላት ደቡብ ሱዳናዊቷ አቲንግ ሙ ፓሪስ ላይ አትሮጥም። ይህም ለተፎካካሪዎቿ መልካም ዜና ሲሆን፤ የአሸናፊነት ፍልሚያውም በእንግሊዝ፣ ኬንያ እና ኢትዮጵያዊቷ አትሌቶች መካከል እንደሚሆን ይጠበቃል።

እንግሊዛዊቷ የቶኪዮ ኦሊምፒክ የብር ሜዳሊያ አሸናፊ ኬሊ ሆኪንሰን፤ በዩጂን እና ቡዳፔስት የዓለም ሻምፒዮናዎች ላይም የብር ሜዳሊያ ማስመዝገቧ የሚታወስ ነው። ኬኒያዊቷ ሜሪ ሞራ ደግሞ በዩጂን የነሐስ ሜዳሊያ ብታጠልቅም በቡዳፔስት ደግሞ የዓለም ሻምፒዮን መሆን ችላለች። ታዲያ ሦስቱ አትሌቶች በተመሳሳይ የእድሜ ክልል ውስጥ ከመገኘታቸውም ባለፈ ያላቸው ፈጣን ሰዓትም እጅግ ተቀራራቢ መሆኑ በታላቁ የኦሊምፒክ መድረክ የወርቅ ሜዳሊያውን አጥልቆ የክብር ባለቤት ለመሆን በመካከላቸው ሊኖር የሚችለው ፍልሚያ ከምሽቱ ተጠባቂ ሁነቶች መካከል አንዱ ነው።